# ክፍል 3

## የተግባራዊ ኑሮ ገለጻ ክፍል፡-

## ጸጋና የክርስቲያን ሕይወት

## ምዕራፍ 5-6

### ገላትያ 5፡1-12

በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንጂ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።

እነሆም እኔ ጳውሎስ እላችኋለሁ፡- ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም። ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ አለበት ብዬ ለሚገረዙት ሁሉ ለእያንዳንዶች ደግሜ እመሰክራለሁ። በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል። እኛ በመንፈስ ከእምነት የጽድቅን ተስፋ እንጠባበቃለንና። በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና። በመልካም ትሮጡ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ ማን ከለከላችሁ? ይህ ማባበል ከሚጠራችሁ አልወጣም። ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል። የተለየ ነገር ከቶ እንዳታስቡ እኔ በጌታ ስለ እናንተ ታምኜአለሁ፤ የሚያናውጣችሁ ማንም ቢኖር ግን ፍርዱን ሊሸከም ነው። ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እስከ አሁን መገረዝን ብሰብክ እስከ አሁን ድረስ ለምን ያሳድዱኛል? እንኪያስ የመስቀል ዕንቅፋት ተወግዶአል። የሚያውኩአችሁ ይቆረጡ።

# - 9 -

## ቁም! ሌባ!

የይሁዲነት አቀንቃኞች እንዲህ ይሉ ነበር፡- «የጳውሎስ የጸጋ መሠረታዊ ትምህርት አደገኛ ነው፤ ሕግን በመተው ለልቅነት ስፍራ ይሰጣል። ለምን! ከሕጋችን ከራቅንና ከፍተኛ መመዘኛችንን ከተውን አብያተ ክርስቲያናችችን ይበታተናሉ።»

በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ መደገፍን የፈሩ የአንደኛው ምዕተ ዓመት የይሁዲነት አቀንቃኞች ብቻ አልነበሩም። በዘመናችንም በአብያተ ክርስቲያናችችን ያሉ ሕጋዊያን በክርስቶስ ስላለን ነጻነት ማውራት ሃይማኖታዊ ሥርዓት አልበኝነት ያመጣል በማለት ያስጠነቅቃሉ። እነዚህ ሰዎች ጳውሎስ ስለ ጸጋ ያስተማረውን ትምህርት በተሳሳተ መንገድ ነው የሚረዱት። ጳውሎስ የዚህን መልእክት የመጨረሻ ክፍል (ገላ. 5-6) የጻፈው ይህን የተሳሳተ ግንዛቤ ለማስተካከል ነበር።

በአሁኑ ትምህርቱ ጳውሎስ የመከራከሪያ አሳብ ከማቅረብ ወደ ሕይወት ተዛምዶ፥ ከእምነት ትምህርት ወደ ተግባራዊ ጉዳይ ተሸጋግሮአል። በእምነት የሚኖር ክርስቲያን ዓመፀኛ ሊሆን አይችልም። ከዚህ በተጻራሪ ውጫዊ ሥርዓት ከሆነው ሰው ሠራሽ ሕግ እጅግ የላቀውን የእግዚአብሔርን ውስጣዊ ሥርዓት ይለማመዳል። በእግዚአብሔር ጸጋ የሚታመን፥ ለእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጠ፥ ለሌሎች የሚኖርና እግዚአብሔርን ለማክበር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ዓመፀኛ መሆን አይችልም። ሕግ አጥባቂው ግን በባርነት ስለሚኖር፥ በሥጋ ስለሚታመን፥ ለራሱ ብቻ ስለሚኖርና የእግዚአብሔርን ክብር ሳይሆን የሰውን ምስጋና ስለሚፈልግ ውሉ ቢያድርም ዓመፀኛ መሆኑ የማይቀር ነው።

ጳውሎስ በጸጋ ስለሚገኘው የክርስትና ነፃነት ያስተማረው መሠረታዊ የእምነት ትምህርት በፍጹም አደገኛ አልነበረም፤ አደገኛ ትምህርት ሕግ አክራሪነት ነው። ምክንያቱም ሕግ አክራሪነት የማይችለውን ለማድረግ ነው የሚሞክረው። አርጌውን ተፈጥሮ ለውጦ ለእግዚአብሔር ሕግጋት እንዲታዘዝ ለማድረግ ይሞክራል። ሕግ አክራሪነት ውጤታማ የሚሆነው ለአጭር ጊዜ ነው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሥጋ ማመፅ ይጀምራል። በመንፈስ

ቅዱስ ኃይል የሚታመን ራሱን የሰጠ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሕግ አይቃወምም፤ ወይም በሕጉ ላይ አያምፅም፤ ይልቁንም ሕጉ በመንፈስ በኩል በሕይወቱ በሥራ ላይ ይውላል (ሮሜ 8፡1-4)። እነዚህን በማጠቃለያዎቹ ምዕራፎች ላይ የሰፈሩትን አሳቦች ቅደም ተከተል መመልከት ቀላል ነው፡-

1. በክርስቶስ ነፃ ወጥቼአለሁ። ከእንግዲህ ወዲህ በሕግ ባርነት ሥር ልሆን አልችልም (ገላ. 5፡1-12)።
2. ሆኖም ሕይወቴን ከውስጥ ሆኖ የሚቆጣጠረኝ አንድ ረዳት ያስፈልገኛል። ይህ ረዳት መንፈስ ቅዱስ ነው (5፡13-26)።
3. በመንፈስ ቅዱስ ፍቅር ለራሴ ሳይሆን ለሌሎች የመኖር ፍላጎት አለኝ (6፡1-10)።
4. ይህ የነጻነት ሕይወት እጅግ መልካም በመሆኑ ለእግዚአብሔር ክብር ልኖረው እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም ይህን ለማድረግ ያስቻለኝ እርሱ ነው (6፡11-18)።

እስቲ ይህን የመሰለውን ሕይወት፥ በሕግና በአንዳንድ ሃይማኖታዊ መሪዎች ሥርዓት ሥር ለመኖር ከመረጠ ሰው ልምምድ ጋር እንደሚከተለው አወዳድር፡-

1. ለእነዚህ ሕጎች ከታዘዝኩ የበለጠ መንፈሳዊ ሰው እሆናለሁ። ይህን ሃይማኖታዊ መሪ እጅግ ስለማደንቀው ለእርሱ መመሪያ እገዛለሁ።
2. ለሕግ ለመታዘዝና ራሴን ለማሻሻል የሚሆን ብርታት እንዳለኝ አምናለሁ። የተነገረኝን በማድረጌም በተወሰነልኝ የሕይወት ብቃት መመዘኛ ላይ እደርሳለሁ።
3. መሻሻል እያደረግሁ ነው። ከዚህ በፊት አደርጋቸው የነበሩትን አንዳንድ ነገሮች አሁን አላደርግም። ባለኝ መታዘዝና የሥነ-ሥርዓት ኑሮ ሌሎች ሰዎች ያመሰግኑኛል። ከሌሎች ጋር ባለኝ ኅብረት ከብዙዎች የተሻልሁ እንደ ሆንሁ ማየት እችላለሁ። በጣም መንፈሳዊ መሆን እንዴት አስደናቂ ነገር ነው።
4. ሌሎች ሰዎች እንደኔ ቢሆኑ ኑሮ እንዴት መልካም በሆነ ነበር። እኔ የእርሱ በመሆኔ እግዚአብሔር ዕድለኛ ነው። ሌሎች እንደ እኔ እንዲሆኑ ይህን ጉዳይ ለሌሎች የማካፈል ከፍተኛ ፍላጎት አለኝ። ቡድናችን እያደገ

ነው። ደግሞም እጅግ መልካም ምስክርነት አለው። ሌሎች ቡድኖች እንደ እኛ መንፈሳዊ ያለመሆናቸው በጣም የሚያሳዝን ነው።

ሕግ አክራሪነትን በየትኛውም መንገድ ብትመለከተው፥ አድብቶ የሚገባና ለጥፋት በምስጢር የሚሠራ አደገኛ ጠላት ነው። ጸጋን ለሕግ ብለህ በምትተውበት ጊዜ ሁሉ ያገኘኸውን ታጣለህ። ጳውሎስ በዚህ የመጀመሪያ ክፍል (5፡ 1-12) የሚገልጸው አማኝ ከእግዚአብሔር ጸጋ ወደሰው ሠራሽ ሕጎችና ደንቦች ሲመለስ ምን እንደሚያጣ ነው።

## 1. ባሪያ ትሆናለህ - አነጋገር ነፃነትህን ታጣለህ(5፡ 1)

ጳውሎስ ሕግ ምን እንደሚመስል ለመልእክቱ አንባቢዎች ለመግለጽ በሁለት ተምሣሌታዊ ማወዳደሪያዎች ከዚህ በፊት ተጠቅሟል፡- በሞግዚት ወይም በበላይ ጠባቂ (3፡24፤ 4፡12-25)፥ በሴት ባሪያ (4፡22-25)። አሁን ደግሞ ከባርነት ቀንበር ጋር ያወዳድረዋል። ጴጥሮስ ይህንኑ ተምሣሌት በታዋቂው የኢየሩሳሌም ጉባኤ ላይ እንደ ተጠቀመበት ታስታውሳለህ (የሐዋ. 15፡ 10 ተመልከት)።

የቀንበርን ምንነት መረዳት አስቸጋሪ አይደለም። ብዙ ጊዜ በሌላ ኃይል የመገዛት፥ የባርነት፥ የአገልግሎትና በቁጥጥር ሥር የመሆንን ጉዳይ ይወክላል። እንደዚሁም ለሌላ አካል በፈቃደኝነት የሚሰጥ አገልግሎትንና መገዛትን ያመለክታል። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነፃ ባወጣ ጊዜ ቀንበር ሰብሮላቸው ነበር (ዘሌ. 26፡ 13)። አንድ ገበሬ በቀንበር የሚጠቀመው የሚያደርስባቸውን በሬዎች ለመምራትና ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ነው። ምክንያቱም ነፃ ቢሆኑ ኖሮ በፈቃደኝነት አያገለግሉም ነበር።

በገላትያ የነበሩ አማኞች በክርስቶስ ባመኑ ጊዜ የኃጢአት ባርነት ቀንበር ተወግዶላቸው የክርስቶስን ቀንበር ተሸከሙ(ማቴ. 11፡28-30)። የሃይማኖት ቀንበር ጠንካራና ሸክሙም እጅግ ከባድ ነው። የክርስቶስ ቀንበር «ልዝብ» ሸክሙም «ቀሊል» ነው። ልዝብ የሚለው የአማርኛ ቃል የግሪክ ትርጉም «ደግ፥ ቸርነትና ጸጋ የተሞላ» ማለት ነው። የክርስቶስ ቀንበር ፈቃዱን እንድናደርግ ነጻ የሚያወጣን ሲሆን፥ የሕግ ቀንበር ግን ትእዛዛትን እንድንፈጽም ባሪያ ያደርገናል። ያልዳነ ሰው የኃጢአትን ቀንበር ይለብሳል (ሰቆ. ኤር. 1፡ 14)፤ ሃይማኖታዊ ሕግ አክራሪ የሆነው ሰው ደግሞ የባርነት

ቀንበር ይለብሳል (ገላ. 5፡ 1)። በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የሚደገፍ ክርስቲያን ግን የክርስቶስን የነጻነት ቀንበር ይለብሳል።

ከሕግ ባርነት ነጻ ያደረገን ክርስቶስ ነው። በመስቀል ላይ በመሞት ከሕግ እርግማን ነፃ አደረገን (ገላ. 3፡ 13)። አንድ ሰው በክርስቶስ ካመነ በኋላ ከጸጋ ሥር እንጂ (ሮሜ 6፡ 14) ከሕግ ቀንበር ባርነት ሥር አይደለም። ይህም ማለት እኛ ከሕግ ውጭ የሆንን ሥርዓተ አልበኞች ወይም ዓመፀኞች ነን ማለት አይደለም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠበቅ በእግዚአብሔር መንፈስ ውስጣዊ አመራር ስላለን ውጫዊ የሆነ የሕግ ኃይል አያስፈልገንም ማለት ነው (ሮሜ 8፡ 1-4)። ክርስቶስ የሞተው ነፃ ሊያወጠን እንጂ ባሪያ ሊያደርገን አይደለም። ወደ ሕግ መመለስ ማለት «አድርግና አታድርግ» በሚሉ ሕጎች ውስብስብ እንቆቅልሾች መታነቅና፥ መንፈሳዊ ጉልምስና ትተን ወደ «ዳግም ሕፃንነት» መመለስ፡ ማለት ነው።

ስለ ነፃነት ምንም ዓይነት ዋስትና የማይሰማቸው አንዳንድ ሰዎች መኖራቸው በጣም የሚያሳዝን ነው። የራሳቸውን ውሳኔ በነፃነት ከማድረግ ይልቅ፥ ለአንዳንድ መሪዎች ጨካኝና አምባ ገነን መመሪያ መታዘዝን ይመርጣሉ። በእግዚአብሔር ጸጋ አማካይነት ባገኙት ነጻነት እጅግ የሚፈሩ አማኞችም አሉ። ስለዚህ ሌሎች ለእነርሱ ውሳኔ እንዲያደርጉላቸው በመፈለግ በሕግ አክራሪነትና በአምባ ገነንነት በሚመራ ቡድን ሥር ይታቀፋሉ። ይህ ለአዋቂ ሰው የሕፃናን ሥራ የሚሠራ ሰውን ይመስላል። የክርስትና ነፃነት መንገድ የክርስቶስ የሙላት መንገድ ነው። ጳውሎስ የሚከተለውን ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የሚያስደንቅ አይደለም። «ጸንታችሁ ቁሙ፥ እንደገና በባርነት ቀንበር አትያዙ»።

## 2. ባለ ዕዳ ትሆናለህ - ሀብትህን ታጣለህ(5፡2-6)

ጳውሎስ ከጸጋ ወደ ሕግ የተመለሰ ክርስቲያን የሚደርስበትን ሦስት ኪሣራዎች ይገልጻል። «ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም» (ቁ. 2)፥ «ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ አለበት» (ቁ. 3)፥ «ከክርስቶስ ተለይታችሁ» (ቁ. 4)። ቀጥሎ ደግሞ በዚሁ በቁ.4 ወደምናገኘው አሳዛኝ ማጠቃለያ እንደርሳለን። «ከጸጋው ወድቃችኋልና።» ሕግ አክራሪነት የአማኝን ነጻነት የሚገፍ መሆኑ በጣም አሳዛኝ ነገር ነው። በተጨማሪ በክርስቶስ ያለውን መንፈሳዊ ብልጥግና ሁሉ ይገፋል። በሕግ ሥር የሚኖር አማኝ የከሰረ ባሪያ ይሆናል።

ጻድቅነትን ባልተቀበልንበት ወቅት ልንከፍለው የማንችለው የእግዚአብሔር ዕዳ እንደ ነበረን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ኢየሱስ በሁለቱ ተበዳሪዎች ታሪክ ይህንን ጉዳይ ግልጽ አድርጎታል (ሉቃስ 7፡36-50)። ሁለቱ ተበዳሪዎች ከአንድ አበዳሪ ገንዘብ ተበደሩ። የአንዱ ተበዳሪ ዕዳ ከሌላኛው አሥር ጊዜ የላቀ ነበር። እነዚህ ተበዳሪዎች መክፈል ስላቃታቸው አበዳሪው የሁለቱንም ዕዳ በታላቅ ችሮታው ተወላቸው። የሰው ልጅ ያለው የሥነ-ምግባር ብቃት ምንም ያህል ከፍተኛ ቢሆንም እንኳ የእግዚአብሔር ክብር ይጎድለዋል። አንድ ሰው ያለበት የኃጢአት ዕዳ ከሌላው ሰው ዕዳ አሥር ጊዜ ቢያንስ እንኳ መክፈል አይችልም። ስለዚህ በእግዚአብሔር የፍርድ መንበር ፊት ተራቁቶ ይታያል። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሠራው ሥራ፥ ዕዳቸው ምንም ያህል ከፍተኛ ቢሆንም እንኳ፥ እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች በጸጋው ይቅርታ ለማድረግ ችሏል።

ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስናምን መንፈሳዊ ባለጠጋ እንሆናለን። ከእግዚአብሔር ጸጋ ባለጠግነት (ኤፌ. 1፡7)፥ ከክብሩ ባለጠግነት (ኤፌ. 1፡18፤ ፊልጲ. 4፡19)፥ ከጥበቡ ባለጠግነት (ሮሜ 11፡33)፥ «ፍለጋ ከሌለው የክርስቶስ ባለጠግነት» (ኤፌ. 3፡8) ተካፋዮች እንሆናለን። በክርስቶስ «የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ» አለን (ቆላ. 2፡3)። እንደዚሁም በእርሱ «ተሞልተናል» (ቆላ. 2፡10)። አንድ ሰው በክርስቶስ ውስጥ ከሆነ ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር የሚፈልገው አይነት የክርስትና ኑሮ ለመኖር የሚያስፈልጉት ነገሮች ሁሉ አሉት።

የይሁዲነት አቀንቃኞች ግን «አንድ ነገር እንደ ጐደለን» እንድናምን ይፈልጋሉ። ይህም ለሕግ ከተገዛንና ሥነ-ሥርዓቶቹንም አክባሪ ከሆንን የበለጠ «መንፈሳዊነት እንደ ጐደለን» እንደምንሆን ነው። ጳውሎስ ግን ምንም ነገር መጨመር ስለማይቻል ሕግ አንዳችም ነገር እንደማይጨምርልን ግልጽ ያደርጋል። በዚህ ምትክ ሕግ እንደ ሌባ አድብቶ በመምጣት አንድ አማኝ በክርስቶስ ያለውን መንፈሳዊ ብልጽግና ይዘርፋል። ከከባድ ኪሣራም ላይ ስለሚጥለው ሊከፍለው ለማይችለው ዕዳ ተጠያቂ ያደርገዋል።

በጸጋ መኖር ማለት ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ብልጽግና መታመን ማለት ነው። በሕግ መኖር ማለት ግን በራስ ብርታት፥ በሥጋ መታመንና ያለ እግዚአብሔር ችሮታ መኖር ማለት ነው። ጳውሎስ (ግርዘት በራሱ ምንም ልዩነት ባያመጣም እንኳ ቁ. 6፤ 6፡15) በዚህ ሁኔታ ግን ለግርዘት ሕግ መገዛት በክርስቶስ ያላቸውን ነፃነት ሁሉ ሊገፍ እንደሚችል

በማሳሰብ የገላትያ ሰዎችን ያስጠነቅቃቸዋል። በተጨማሪም ለአንዱ ሕግ መገዛት ሕግጋትን በሙሉ እንዲፈጽሙ ግዴታ ውስጥ የሚከት ነበር።

ሕግ አክራሪዎች ከሕግጋቱ አንዳችም ሳያስቀሩ በፍጹምነት መጠበቅ ስለማይችሉ ግብዝነታቸው እዚህ ላይ ይጋለጣል። በእነርሱ ዘንድ የብሉይ ኪዳን ሕግ ተፈጻሚነት የሚያገኘው፥ አንድ ደንበኛ ምግብ ቤት ውስጥ ያሉ የተለያዩ ምግቦችን ተመልክቶ የሚፈልገውን ከወሰደ በኋላ የቀሩትን ለመተው ባለው ምርጫ መልክ ነበር። ይህ ደግሞ ታማኝነት የጐደለው ምግባር ይሆናል። ለምሳሌ፡- በዚህ ዘመን ያለ ክርስቲያን የሞት መቅሠፍት የማለፍ (ፋሲካ) በዓልን ባያከብርም እንኳ፥ ሰንበትን ማክበር አለበት ማለት የእግዚአብሔርን ሕግ መነጣጠል ነው። ሕግጋትን ሁሉ የሰጠው አንዱ እግዚአብሔር ነው (ያዕ. 2፡9-11)። ከዚህ ቀደም ብሎ ጳውሎስ፥ ሕግጋትን በሙሉ አንዳችም ሳያስቀሩ በማይጠብቁ ሁሉ ላይ የሕግ መርገም በላያቸው ላይ እንዳለ በማረጋገጥ ሙሴን ጠቅሶ ነበር (ገላ. 3፡10፤ ዘዳ. 27፡26 ተመልከት)።

ይህን ለማብራራት ያህል እስቲ አንድ የመኪና አሽከርካሪ በከተማ ውስጥ እያሽከረከረ ሳለ አውቆም ይሁን ሳያውቅ ቀይ መብራት ጥሶ ሄደ እንበል። የትራፊክ ፖሊስ ይይዘውና የመንጃ ፈቃዱን ይጠይቀዋል። ወዲያውኑ ይህ ሾፌር ራሱን በመከላከል «እባክዎን ቀይ መብራት እንደ ጣስሁ አምናለሁ፤ ነገር ግን ማንንም ዘርፌ አላውቅም፤ በሕይወት ዘመኔ ሁሉ አመንዝሬ አላውቅም፤ ግብር አከፋፈልም ላይ አታልዬ አላውቅም» እያለ ቢለፈልፍ የትራፊክ ፖሊሱ ግን ፈገግ በማለት የክስ መጥሪያውን ይጽፍለታል። ምክንያቱም በብዙ ነገሮች ታዛዥ መሆን በአንድ ነገር እንኳ ያለመታዘዝን ጥፋት ሊያካክሰው ስለማይችል ነው። ጥፋተኛው ሰው እንዲቀጣ ታዛዥ የሆነው ሰው ደግሞ ጥበቃ እንዲያገኝ የሚያደርግ ያው አንድ ሕግ ነው። የሕግን የተወሰነ ክፍል እየተላለፉ የተቀሩትን ክፍሎች ደግሞ እየጠበቅሁ ነው ብሎ መመካት፥ ቅጣት የሚገባኝ ነኝ በማለት እንደማወጅ ነው የሚቆጠረው።

ጳውሎስ «ከጸጋው ወድቃችኋል» ሲል ምን ማለቱ እንደ ነበር አሁን በተሻለ ሁኔታ ልንረዳው እንችላለን (ገላ. 5፡4)። በዚህ አባባሉ የገላቲያ ሰዎች «ደህንነታቸውን አጥተዋል» ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ምክንያቱም ጳውሎስ በዚህ መልእክት ውስጥ በአጠቃላይ ስለ ገላትያ ሰዎች ሲናገር ክርስቲያን መሆናቸውን በመቀበል ነበር። ቢያንስ ዘጠኝ ጊዜ ያህል

«ወንድሞች» እያለ ይጠራቸዋል። ደግሞም «እኛ» በሚለው «ተውላጠ ስም» ተጠቅሟል (4፡28፥31)። መልእክቱን የሚያነቡ ሰዎች አማኞች ባይሆኑ ኖሮ ጳውሎስ በእነዚህ አባባሎች ፈጽሞ አይጠቀምም ነበር። በተጨማሪም «ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኸውን የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ» (4፡6) ብሏል። ስለዚህ መልእክቱን የሚያነቡት ሰዎች ያልዳኑ ቢሆን ኖሮ ጳውሎስ እንደዚህ ለማለት ባልደፈረም ነበር።

በመሆኑም «ከጸጋው መውደቅ» ማለት ደህንነትን ማጣት ማለት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጸጋ ክልል ውጭ መውደቅ ማለት ነው። ጸጋና ሕግን መደባለቅ አትችልም። በሕግ ክልል ለመኖር ከወሰንህ በጸጋ ክልል መኖር አትችልም። በገላትያ የነበሩ ክርስቲያኖች ሐሰተኛ አስተማሪዎች አዚም አድርገውባቸው ነበርና (ገላትያ 3፡1)፤ በዚህ ምክንያት ለእውነት አይታዘዙም ነበር። ወደ ሌላ ወንጌል ዞር በማለት (1፡6-9) ወደ ቀድሞ ሃይማኖት የመጀመሪያ ነገሮች ተመልሰው ነበር (4፡9)። የዚህም ውጤት በባርነት ቀንበር መታነቃቸውና አሁን ባሉበት ሁኔታ «ከጸጋ ወድቀው» መገኘታቸው ነበር። የዚህ ውድቀት አሳዛኝነቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያደርግላቸው የሚችለውን መልካም ነገሮች ሁሉ ከራሳቸው ላይ ገፍፈው መጣላቸው ነው።

ጳውሎስ ቀጥሎ ያቀረበው፥ አማኝ በጸጋ ክልል ውስጥ የሚኖረውን ሕይወት ነው (5፡5-6)። ይህ ክፍል ሁለቱን የሕይወት መንገዶች እንድናነጻጽር ይረዳናል። በጸጋ ስትኖር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ትደገፋለህ። በሕግ ስትኖር ግን በራስህና በጥረትህ መደገፍህ ነው። እምነት ሕያው ሆኖ የሚሠራ እንጂ የሞተ አይደለም (ያዕ. 2፡14-26)። እምነት በመንፈስ ቅዱስ በኩል ስኬታማ ሊያደርግ የሚችለውን የሥጋ ጥረት ሊያደርገው አይችልም። እምነት የሚሠራው በፍቅር ነው። ይህ ፍቅር ለእግዚአብሔርና ለሌሎች ያለው ፍቅር ነው። ሥጋ ደግሞ ብዙ ጊዜ ስስታምነትንና ተቀናቃኝነትን እንጂ ፍቅርን ሊያመነጭ አይችልም (ገላ. 5፡15 ተመልከት)። ጳውሎስ የሕግ አክራሪነትን ሕይወት በውድቀት መስሎ ማቅረቡ የሚያስደንቅ አይሆንም።

አንድ አማኝ በእግዚአብሔር መንፈስ ላይ በመደገፍ በእምነት በሚራመድበት ጊዜ በእግዚአብሔር ጸጋ ክልል ውስጥ ስለሚኖር የሚያስፈልገውን ሁሉ ያገኛል። የእግዚአብሔርን ጸጋ ባለጸግነት

ይለማመዳል። ሁልጊዜ ወደፊት የሚጠብቀው ተስፋ ይኖረዋል (5፡5)። ይህም ኢየሱስ እንደ ራሱ ፍጹም ጻድቅ ሊያደርገን አንድ ቀን የመመለሱ ተስፋ ነው። ሕግ የፍጹም ጻድቅ የወደፊት ተስፋን አይሰጥም። ሕግ ለክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት መንገድ አዘጋጅቷል (3፡23-4፡7)። ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት መንገድን ሊያዘጋጅ ግን አይችልም።

ስለዚህ ሕግ አክራሪነትን የሚመርጥ አማኝ መንፈሳዊ ነፃነቱንና ብልጽግናውን ከራሱ ላይ ይገፍፋል። እያወቀ ራሱን ከባርነት ቀንበር ሥርና ከኪሳራ ላይ ይጥላል።

## 3. እንደ ሯጭ - አቅጣጫህን ትስታለህ (5፡7-12)

ጳውሎስ ሯጮችን በምሳሌ የመጠቀም ልማድ ስላለው ብዙ ጊዜ በመልእክቶቹ ያነሣቸዋል። የመልእክቶቹ አንባቢዎች የነበሩት የገላትያ ሰዎች የኦሎምፒክ ጨዋታዎችንና ሌሎችንም የሩጫ እሽቅድምድሞችን የሚያካትቱ የግሪኮችን ውድድሮች ይመለከቱ ነበር። ጳውሎስ በእነዚህ ውድድሮች ተምሣሌነት የተጠቀመው ስለ ደህንነት ለመናገር እንዳልሆነ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ለክርስቲያኖች ሁልጊዜም የሚናገረው የክርስትናን ሕይወት እንዴት መኖር እንዳለባቸው ነው። በግሪክ ውድድሮች ለመሳተፍ የመጀመሪያው ቅድመ ሁኔታ ዜግነት ነበር። እኛም በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የሰማያዊቷ አገር (የመንግሥተ ሰማያት) ዜጋ ሆነናልና ሮጠን እናሸንፍ ዘንድ ጌታ ከውድድሩ አስገብቶናል። ይኸውም የምንሮጠው ሽልማትን ለማግኘት ነው ማለት ነው (ፊልጵ. 3፡12-21)። ስለዚህ የምንሮጠርው ደህንነትን ስላገኘንና በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም (የሐዋ. 20፡24) ስለምንፈልግ እንጂ ደህንነትን ለማግኘት አይደለም።

«በመልካም ትሮጡ ነበር»። ጳውሎስ መጀመሪያ ወደ እነርሱ በመጣ ጊዜ የተቀበሉት «እንደ እግዚአብሔር መልአክ ነበር» (ገላ. 4፡14)። ቃሉን በመቀበልና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ነበር። ሁሉም ሰው የሚያየው ጥልቅ የሆነ ደስታ ይታይባቸው ነበር። ከጳውሎስ ላለመለየትና ማንኛውንም መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ነበሩ (4፡15)። አሁን ግን ጠላታቸው መስሎ ታያቸው። ለዚህ ምክንያቱ ምን ይሆን?

የቁጥር 7 ቀጥተኛ ትርጉም ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሰጠናል። «በመልካም ትሮጡ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ ማን ከለከላችሁ?» በሩጫ ውድድር ውስጥ እያንዳንዱ ሯጭ የሚሮጥበት ጠባብ መንገድ በመስመር ተለይቶ ይሰጠዋል። አንዳንድ ሯጮች ተፎካካሪዎቻቸውን ከውድድር ለማስወጣት መስመሩን እንዲለቁ ለማድረግ መሰናክል ይፈጥሩባቸው ነበር። የይሁዲነት አቀንቃኞችም በገላትያ ሰዎች ላይ ያደረጉት መፈታተን ከዚህ ተለይቶ የሚታይ አልነበረም። የውድድር መስመራቸውን በማቋረጥ አቅጣጫቸውን እንዲለውጡ አስገደዷቸውና ከዋናው መንፈሳዊ መንገድ ለቀው በሌላ መንገድ እንዲሄዱ አደረጓቸው። ይህን ያደረገው እግዚአብሔር አልነበረም፤ ምክንያቱም እርሱ የጠራቸው በተሰመረላቸው «የጸጋ» መስመር እንዲሮጡ ነበር።

የጳውሎስ ገለጻ ከሩጫ ውድድር ወደ ምግብ ማብሰል ምሳሌነት ይሸጋገራል፤ በዚህ ስፍራ ስለ እርሾ ይናገራል። በብሉይ ኪዳን እርሾ የክፋት ምሳሌ ነው። ለምሳሌ፡- የሞት መቅሠፍት ባለፈበት ወቅት የፋሲካ በዓል ሲከበር እርሾ እንዲኖር አልተፈቀደም ነበር (ዘጸ. 12፡15-19፤ 13፡7)። ለአንዳንድ የተለዩ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ከመሥዋዕቱ ጋር እርሾ እንዳይደባልቁ ታግደው ነበር (ዘጸ. 34፡25)። ኢየሱስ እርሾን የኃጢአት ተምሳሌት አድርጎ በመጠቀም «ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ» በማለት አስጠንቅቋል (ማቴ. 16፡6-12)። ጳውሎስ ደግሞ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ኃጢአት ለመግለጥ እርሾን በተምሳሌነት ጠቅሶአል (1ኛ ቆሮ. 5)።

እርሾ ጥሩ የኃጢአት ተምሳሌት ነው። ትንሽ ቢሆንም እንኳ ቀስ በቀስ ሁሉን ይበክላል። የይሁዲነት አቀንቃኞች ሐሰተኛ ትምህርት ወደ ገላትያ ቤተ ክርስቲያን የገባው በትንሹ ነበር፤ ብዙ ሳይቆይ ግን «እርሾው» ሁሉንም ለመበከልና ለመቆጣጠር ቻለ።

የሕግ አክራሪነት መንፈስ በቤተ ክርስቲያን ላይ የበላይነት የሚይዘው በድንገት አይደለም። እንደ እርሾ በምስጢር ይገባና ያድጋል፤ ብዙ ሳይቆይ አጠቃላይ ጉባኤውን ይመርዛል። ብዙ ጊዜ ሕግ አክራሪነትን እንዲነግሥ የሚያደርጉት ውስጣዊ ምክንያቶች መልካም ናቸው፡- (ለምሳሌ «ከዚህ የተሻለ መንፈሳዊ ቤተ ክርስቲያን እንፈልጋለን»)። የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም።

በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መመዘኛዎች መኖራቸው ስህተት አይደለም። ሆኖም እነዚህ መመዘኛዎች ማንኛውንም ሰው መንፈሳዊ ያደርጋሉ ብለን ልናስብ ግን አይገባም። ወይም መመዘኛዎችን ማሟላት የመንፈሳዊነት ማስረጃ ነው ብለን ልንቀበለው አይገባም። እርሾው ሲያድግ በቀላሉ ነው። ብዙ ሳይቆይ ስለ መንፈሳዊነታችን መመካት እንጀምራለን (በ1ኛ ቆሮ. 5፡2 ጳውሎስ እዚህ ላይ ያስቀመጠው «ማበጥ» ወይም መወጠር የሚል ቃል ነው)። እርሾ የሚያደርገው ይህንኑ ነው። «ያሳብጣል ወይም ይነፋል።» የሌሎች ሰዎችን መንፈሳዊ አለመሆን መተቸት እንጀምራለን። ይህ በእርግጥ ሥጋን ብቻ የሚመግብና መንፈስን የሚያሳዝን ነው። እግዚአብሔርን የምናከብር እየመሰለን በራሳችን መንገድ መሄዳችን ነው።

እያንዳንዱ ክርስቲያን የሕግ አክራሪነትን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማቆጥቆጥ የመከታተል ኃላፊነት አለበት። እንደ እርሾ ያነሰው ነገር ያድግና በክርስቲያናዊ ኅብረት ውስጥ ትልቅ ችግር ያስከትላል። ጳውሎስ ሐሰተኛ አስተማሪዎችን በሚያወግዝበት ጊዜ ኃይለኛ መራራ ቃል መጠቀሙ የሚያስደንቅ አይደለም። «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና መገረዝን ብሰብክ እስካሁን ድረስ ለምን ያሳድዱኛል? እንኪያስ የመስቀል እንቅፋት ተወግዷል። የሚያውኳችሁ ይቆረጡ» (ገላ. 5፡11-12)።

ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ወዲህ ግርዘት ምንም አይነት መንፈሳዊ ዋጋ የሌለው ውጫዊ ተግባር ብቻ ነው። ጳውሎስ ሐሰተኛ አስተማሪዎች በራሳቸው ላይ ቀዶ ጥገና ሊያካሂዱ ወይም ራሳቸውን ቢሰልቡ ይሻላቸው ነበር ይላል። ይህን የተመኘው ተጨማሪ «የባርነት ልጆች» ማፍራት እንዳይችሉ ነበር።

በእግዚአብሔር ጸጋ ክልል የሚኖር አማኝ ነፃ፥ ባለጸጋና ወደ ሽልማት ሙላት በሚያደርሰው ጠባብ መንገድ ላይ የሚጓዝ ነው። ጸጋን ለሕግ የተወ አማኝ ግን ባሪያ፥ ድሃና በትክክለኛው መንገድ ወጥቶ ባልተፈቀደ መንገድ የሚጓዝ ነው። በአጭሩ ተሸናፊ ነው። አሸናፊ የመሆኛ ብቸኛው መንገድ ሕግና ጸጋን የሚያደባልቁ የሐሰተኛ አስተማሪዎችን የትምህርት «እርሾ ማስወገድ ነው»። ራስን ለመንፈስ ቅዱስ መስጠት ነው።

የእግዚአብሔር ጸጋ በሕይወት ለሚያስፈልጉን ነገሮች ሁሉ ብቁ ነው። በጸጋው ድነናልና (ኤፌ. 2፡8-10)፤ በጸጋ እናገለግላለን (1ኛ ቆሮ. 15፡9-10)። ጸጋ በመከራ እንድንጸና ያስችለናል (2ኛ ቆሮ. 12፡2)። ድል

ነሺ ወታደሮች እንድንሆን የሚያጠነክረን ጸጋ ነው (2ኛ ጢሞ. 2፡1)። አምላካችን የጸጋ ሁሉ አምላክ ነው (1ኛ ጴጥ. 5፡10)። ወደ ጸጋው ዙፋን በመቅረብ ለሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ጸጋን ማግኘት እንችላለን (ዕብ. 4፡16)። «የጸጋው ቃል» (የሐዋ. 20፡32) የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ፥ የጸጋው መንፈስ (ዕብ. 10፡29) በክርስቶስ ምን ያህል ባለጠጎች እንደ ሆንን ይገልጽልናል።

«እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል» (ዮሐ. 1፡16)።

የቱን ያህል ባለጠጎች ነን!!

## ገላትያ 5፡ 13-26

ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለአርነት ተጠርታችኋል፤ ብቻ አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን አይስጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በእርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ። ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና፥ እርሱም፡- ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው። ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላሉ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ።

ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ። ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም። የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኩሰት፥ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።

በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ። እርስ በርሳችን እየተነዛዛንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ።

# - 10 -
## አምስተኛው ነፃነት

ፕሬዝዳንት ፍሬንክሊን ዲ ሩዝቬልት፥ ጥር 6 ቀን 1941 ዓ.ም. ለምክር ቤቱ ባደረጉት ጠቃሚ ንግግር ላይ ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ እንዲኖር ስለሚመኙት ዓለም የነበራቸውን ራእይ ሲያካፍሉ፥ ሰዎች ሁሉ ሊለማመዷቸውና ሐሴት ሊያደርጉባቸው ስለሚገባ አራት መሠረታዊ ነፃነቶች ተናግረው ነበር። እነዚህም፥ የንግግር ነፃነት፥ የአምልኮ ነፃነት፥ የመሠረታዊ ፍላጎት ነፃነትና ከፍርሃት ነፃ መሆን ናቸው። እነዚህ ነፃነቶች በ1941 ዓ.ም. ከነበሩበት ሁኔታ ይልቅ አሁን በተሻለና በላቀ ደረጃ ተግባራዊ ሆነዋል። ዓላማችን ግን ሌላ አምስተኛ ነጻነትን ትፈልጋለች። ሰው ከራሱና ከጨካኙ የኃጢአት ተፈጥሮው ቀንበር ነጻ መሆን ያስፈልገዋል።

ሕግ አክራሪዎች ከሕጎችና ከማስጠንቀቂያዎች ሥር ላሉ ችግሮች መፍትሔ እንዳላቸው ይናገራሉ። ጳውሎስ ግን ማንኛውም ሕግ የሰውን መሠረታዊ የኃጢአት ተፈጥሮ መለወጥ እንደማይችል ይገልጻል። ለውጥ የሚያመጣው ከውጭ ያለ ሕግ ሳይሆን ከውስጥ ያለ ፍቅር ነው። ከውስጣችን የሚመነጭ ሌላ ኃይል ያስፈልገናል። ይህ ኃይል የሚመጣው ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በገላትያ መጽሐፍ ቢያንስ 14 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። በክርስቶስ ስናምን መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ለማደር ይመጣል (3፡2)። እንደ ይስሐቅ ሁሉ የተወለድነው በመንፈስ ነው (4፡29)። ለደኅንነታችን ዋስትና የሚሰጠን በውስጣችን ያለው መንፈስ ሲሆን (4፡6) ለክርስቶስ እንድንኖርና እርሱን እንድናከብር የሚያስችለን መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ የመለኮታዊ ኃይል ተጽዕኖ ብቻ ሳይሆን እንደ አብና ወልድ መለኮታዊ አካል ነው። እግዚአብሔር አብ ያቀደልህንና እግዚአብሔር ወልድ በመስቀል ላይ ያደረገልህን፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በግል ሕይወትህ ውስጥ ተግባራዊ ያደርግልሃል።

ከገላትያ መጽሐፍ የመዝጊያ ክፍል ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆነው አንቀጽ ይህ ነው። ምክንያቱም ጳውሎስ አንድ አማኝ በክርስቶስ ባገኘው

ነፃነት ሐሴት እንዲያደርግ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን ሦስት አገልግሎቶች የገለጸው በዚህ ክፍል ነው።

## 1. መንፈስ ቅዱስ የፍቅርን ሕግ እንድንፈጽም ያስችለናል (5፡13-15)

የእኛ ዝንባሌ በያዝናቸው ጉዳዮች ላይ በአንድ አቅጣጫ ርቆ መሄድ ነው። አንዳንድ አማኝ ነፃነትን በተሳሳተ መልኩ ስለሚረዳው የፈለገውን ሁሉ ማድረግ እንደሚችል ያስባል። ሌላው አማኝ ደግሞ ይህንን ስህተት በመመልከት በሰዎች ሁሉ ላይ ሕጎችን ይጭናል፤ እንዲፈጽሙአቸውም ያስገድዳል። እውነተኛው ክርስቲያናዊ ነፃነት የሚገኘው እንደ ልብ በመኖርና በሕግ አክራሪነት መካከል ባለው ሚዛናዊ በሆነ ነጥብ ላይ ነው።

ስለዚህ ጳውሎስ ጥሪያችንን በመግለጽ ይጀምራል። የተጠራነው ወደ ነጻነት ነው። ክርስቲያን በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ይቅር ባይነት ስለ ተለማመደ በኃጢአት ተጠያቂ ከመሆን ፍጹም ነፃ ነው። እንደዚሁም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለ ሞተለት ከኃጢአት ቅጣት ነፃ ነው። ኃጢአት በዕለታዊ ሕይወቱ ከነበረው ኃይል በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነፃ ሆኗል። ደግሞም ሕግ ከሚጠይቃቸው ጉዳዮችና ከማስፈራሪያዎቹ ሁሉ ነፃ ነው። ክርስቶስ የሕግን መርገም በመሸከሙ የሕግን ጨካኝ አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ አስወግዷል። የተጠራነው «በክርስቶስ ጸጋ» ስለ ሆነ ነፃነትን አግኝተናል (ገላ.1፡6)። ጸጋና ነፃነት በአንድነት የሚሄዱ ጉዳዮች ናቸው።

ጳውሎስ ጥሪያችንን በሚገባ ካስረዳ በኋላ «አርነታችሁ ለሥጋ ምክንያት እንዳይሰጥ ተጠንቀቁ!» በማለት ያሳስባል።

የእግዚአብሔር ጸጋ እውነተኛ ትርጉም ያልገባቸው ሰዎች ሁሉ ፍርሃት ይህ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። «ሕግጋትንና ደንቦችን ከተውን ሥርዓተ አልበኝነትንና ዐመፅን እንፈጥራለን» ይላሉ።

እንደዚህ አይነቱ አደጋ መኖሩ እርግጥ ነው። ምክንያቱ ግን የእግዚአብሔር ጸጋ ብቃት ስላጣ ሳይሆን ሰው ከእግዚአብሔር ጸጋ በመጉደሉ ሰው (ዕብ. 12፡15)። «እውነተኛ የእግዚአብሔር ጸጋ» ተብሎ የሚጠቀስ ነገር ካለ (1ኛ ጴጥ. 5፡12) ሐሰተኛ የሚባል የእግዚአብሔር ጸጋ ደግሞ አለ ማለት ነው። «የአምላክን ጸጋ በሴሰኝነት» ለመለወጥ የልቅነት ፈቃድ አድርገው (ይሁዳ 4) የሚጠቀሙበት ሐሰተኛ አስተማሪዎች አሉ።

ስለዚህ የጳውሎስ ማስጠንቀቂያ ዋጋ ያለው ነው። የክርስቲያን ነጻነት ኃጢአትን የማድረጊያ ፈቃድ ሳይሆን ሌሎችን ለማገልገል የሚያስችል ዕድል ነው።

ይህ ወደ አንድ ትእዛዝ ይመራናል:- «በፍቅር እርስ በእርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ» (ገላ. 5፡13)። ቁልፍ ቃሉ ፍቅር መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ቀመሩ የሚከተለውን ይመስላል:-

ነፃነት + ፍቅር = ለሌሎች አገልግሎቶች ማበርከት

ነፃነት — ፍቅር = የልቅነት ፈቃድ (የኃጢአት ባርነት)

ካርል የተባለ ሰው ወደ ኩሽና እየገባ ለሚስቱ እንዲህ አላት:- «በዚህ ሳምንት ተጨማሪ የእረፍት ቀን አለኝ። በዚህ ቀን የዶንን ቢስኪሌት ለማስተካከልና ላሪን ሲያወራው ወደ ነበረው ሙዚየም ይዤ በመሄድ ለማሳለፍ አስቤአለሁ።»

ሚስቱ ግን «አንድ ቢስክሌት ማስተካከልና ወደሙዚየም መሄድ የእረፍት ቀንን በደስታ የማሳለፊያ መንገድ አይመስለኝም» አለችው።

ካርል መልሶ «ልጆቹን ለሚውድ ሰው ይህ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው» አላት።

ስለ ፍቅር ያለው አስደናቂ ነገር፥ እግዚአብሔር እስካሁን የሰጣቸውን ሕግጋት በሙሉ የሚያካትት መሆኑ ነው። «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» የሚለው ቃል በሰዎች ኅብረት ውስጥ የሚኖረውን ማንኛውንም ችግር ያቃልለዋል (ሮሜ 13፡8-14 ተመልከት)። ለክርስቶስ ካለህ ፍቅር የተነሣ ሰዎችን የምትወድ ከሆነ አትሰርቃቸውም፤ ስለ እነርሱ ሐሰተኛ ነገር አትናገርም፤ አትቀናባቸውም ወይም በምንም መንገድ የሚገዳቸውን ነገር አታደርግም። እግዚአብሔር ሕግንና ሕግ የሚያስከትላቸውን ማስፈራሪያዎች ሁሉ የተካው ከልብ በሚመነጭ ፍቅር ነው።

ልጆቻችን ትናንሾች በነበሩ ጊዜ የምንኖረው ተሽከርካሪዎች በሚበዙበት አውራ ጎዳና አጠገብ ነበር። ወደ መንገዱ አጠገብ ከደረሱ እንደምንቀጣቸው ያውቁ ነበር። እያደጉ በሄዱ ቁጥር ደግሞ መታዘዝ ሽልማትን እንደሚያስገኝ ተማሩ። ስለዚህ መታዘዝ ከቅጣት ለማምለጥ ብቻ ሳይሆን ደስታን ለማግኘት ጭምር እንደሚያስችል ተረዱ። ዛሬ የምንኖረው በጣም ሥራ የሚበዛባትና አደገኛ በሆነች ከተማ ነው። ከልጆቻችን አንዳንዶቹ መኪና ያሽከረክራሉ። ሆኖም አደጋ ላይ እንዳይወድቁ ልናባብላቸውም ሆነ ልናስፈራራቸው

አያስፈልገንም። ሕይወታቸውን የሚቀጣጠር በፍቅር ላይ የተገነባ ሥነ ሥርዓት ስላላቸው፥ ሆነ ብለው ራሳቸውንም ሆነ ወላጆቻቸውን ወይም ሌሎችን የሚጎዳ ተግባር አያደርጉም። ፍቅር ሕግን ተክቷል።

ጉዳዩን በከፍተኛ ደረጃ ስናየው በውስጣችን ያለው መንፈስ ቅዱስ የሚያስፈልገንን ፍቅር ይሰጠናል (ሮሜ 5፡5፤ ገላ. 5፡6፥22)። የገላትያ አማኞች ይህ አይነቱ ፍቅር ተለይቷቸው እርስ በርሳቸው «ሲነካከሱና ሲበላሉ» ስለ ነበር የመጠፋፋት አደጋ ላይ ነበሩ (ገላ. 5፡15)። በዚህ ቦታ በተምሳሌነት የቀረበው እርስ በርሳቸው የሚጠቃቁ አውሬዎች ሁኔታ ነበር። ይህ ራሱ ሕግ ሰዎች በአንድነት ተስማምተው እንዲሄዱ የማድረግ አቅም እንደሌለው ማረጋገጫ ነው። አንዲት ቤተ ክርስቲያን ምንም ያህል ሕግጋትንና መመዘኛዎችን ብታበጅ እነዚህ ነገሮች የመንፈሳዊነት ዋስትና አይደሉም። የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ልባችንን በፍቅር እንዲሞላ ካልፈቀድን በስተቀር ስስታምነትና ባላንጣነት በመካከላችን ይነግሣል። በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት የነበሩ አክራሪዎችም ሆኑ ሥርዓት አልበኞች የክርስቲያኖችን ኅብረት እያጠፉና እያበላሹ ነበር።

መንፈስ ቅዱስ የሚሠራው በባዶ ሜዳ አይደለም። በክርስቶስ እኛን ያንጽና ይገነባ ዘንድ በእግዚአብሔር ቃል፥ በጸሎት፥ በአምልኮና በአማኞች ኅብረት ይጠቀማል። በየዕለቱ የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብና ለጸሎት በቂ ጊዜ የሚመድብና ለመንፈስ ቅዱስ ሥራ ራሱን የሚሰጥ አማኝ በነጻነቱ ሐሴት በማድረግ ቤተ ክርስቲያንን ለመገንባት ታላቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ጳውሎስ በጸጋ የመንፈሳዊ አገልግሎትና በሕግ የሥጋ አገልግሎት መካከል ስላለው ልዩነት የሰጠውን መግለጫ ከ2ኛ ቆሮ. 3 ላይ አንብብ።

## 2. መንፈስ ቅዱስ ሥጋን እንድናሸንፍ ያደርገናል (5፡16-21፥24)

አንዱ በሌላው ላይ ያለው ተቃውሞ (አምባጓሮ) (5፡16-17)፡- ይስሐቅና እስማኤል በአንድነት መኖር እንዳልቻሉ ሁሉ መንፈስና ሥጋ (አሮጌ ተፈጥሮ) እርስ በርሳቸው በተቃውሞና በጦርነት ላይ ናቸው። ጳውሎስ «ሥጋ» ሲል ውጫዊ አካላችንን ማለቱ እንዳይደለ የተረጋገጠ ነው። የሰው አካል ኃጢአተኛ አይደለም። ክፉ ወይም በጎ ሊደረግበት የሚችል መካከለኛ ነው። አካላችንን የሚቆጣጠረው መንፈስ ቅዱስ ከሆነ በመንፈስ እንመላለሳለን። አካላችንን የሚቆጣጠረው ግን ሥጋ ከሆነ በሥጋ ምኞትና

ፍላጎት እንመላለሳለን። በመንፈስና በሥጋ መካከል ያለው ተቃውሞ ምክንያት መንፈስና ሥጋ የተለያዩ ፍላጎቶች ያላቸው መሆናቸው ነው።

እነዚህ ተቃራኒ ፍላጎቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ መንገዶች ተገልጸዋል። ለምሳሌ፡- በግ ቆሻሻ ነገሮችን የማይወድ ንጹህ እንስሳ ሲሆን፥ አሳማ ግን ከታጠበች በኋላ ወደ ጭቃ የምትመለስ ንጽሕናን የማትወድ ናት (2ኛ ጴጥ. 2፡19-22)። ዝናቡ መዝነቡን አቁሞ መርከቡ በሚገባ ተደላድሎ ከቆመ በኋላ ኖህ አንድ ቁራ ሰድዶ ነበር፤ ቁራው ግን አልተመለሰም (ዘፍ. 8፡6-7)። ቁራ ሥጋ በል እንደ መሆኑ በቂ ምግብ በማግኘቱ በዚያው ቀረ። ኖህ ከንጹሕ አእዋፍ አንዷ የሆነችውን እርግብን በለቀቀ ጊዜ ግን ተመልሳ መጣች (ዘፍ. 8፡8-12)። ለመጨረሻ በለቀቃት ጊዜ ግን አልተመለሰችም። ይህ ማለት ልታርፍበት የምትችልበት ደረቅ መሬት አገኘች ማለት ነበር። ስለዚህ ውኃው ቀንሶ ነበር።

አሮጌው ተፈጥሮአችን ሁልጊዜ ንጹሕ ያልሆነን ነገር ለምግብነት በሚፈልጉት አሳማና ቁራ ይመስላል። አዲሱ ተፈጥሮአችን ደግሞ ንጹህና ቅዱስ የሆኑትን ነገሮች አጥብቀው እንደሚፈልጉት ርግብና በግ አይነት ነው። ስለዚህ በአማኙ ሕይወት ውስጥ ትግል ቢካሄድ ምንም አያስደንቅም። የማያምነው ሰው ግን መንፈስ ቅዱስ ስለሌለው (ሮሜ 8፡9) ስለዚህ ጦርነት የሚያውቀው አንዳችም ነገር አይኖርም። እስማኤል፥ ይስሐቅ እስከሚወለድ ድረስ አንዳችም ችግር አልፈጠረም ነበር።

ክርስቲያን ሥጋን ድል መንሣት የሚችለው ውሳኔ ስላደረገ ብቻ እንዳይደለ ልብ በል። «እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ። ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም» (ገላ. 5፡17)። ጳውሎስ በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ የሚናገረው ይህንኑ ችግር ነበር። «የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም።...የማልወደውን ክፉ ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎ ነገር አላደርገውም» (ሮሜ 7፡15፥19)። ጳውሎስ ድል መኖሩን አልካደም። በእነዚህ ጥቅሶች ያስተላለፈው መልእክት ይህንን ድል በራሳችን ብርታትና ፈቃድ ልናገኘው ያለመቻላችንን ነው።

ድሉ (5፡18)፡- የችግሩ መፍትሄ ፈቃዳችንን ከሥጋችን ፍላጎት ጋር ማዋጋት ሳይሆን ፈቃዳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ማስገዛት ነው። የዚህ ቁጥር ቀጥተኛ ትርጉም «በፈቃዳችሁ በመንፈስ ቅዱስ ብትመሩ ከሕግ በታች አይደላችሁም» የሚል ነው። መንፈስ ቅዱስ በፍቅር እንድንታዘዘው

የእግዚአብሔርን ሕግ በልባችን ላይ ይጽፋል። (ዕብ. 10፡14-17፤ 2ኛ ቆሮ. 3 ተመልከት)። «አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ፤ ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው» (መዝ. (40)፡8)። በመንፈስ ቅዱስ መመራትና «በመንፈስ መመላለስ» ለሥጋ ፈቃድ ራስን የመስጠት ተቃራኒ ነው።

መስቀሉ (5፡19-21፥24)፡- ጳውሎስ እጅግ መጥፎ የሆኑትን አንዳንድ የሥጋ ሥራዎች ይዘረዝራል። (በማር. 7፡20-23፤ ሮሜ 1፡29-32፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡9-10፥ 2ኛ ጢሞ. 3፡2-5 ተመሳሳይ መዘርዝሮችን ታገኛለህ።) ሥጋ ኃጢአትን ማመንጨት እንጂ የእግዚአብሔርን ጽድቅ በፍጹም ሊያፈራ አይችልም። «የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ እጅግም ክፉ ነው» (ኤር. 17፡9)። በገላትያ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጠው መዘርዝር በሦስት ዋና ክፍሎች ሊከፈል ይችላል።

(1) የፍትወት ኃጢአቶች (5፡19፥21)

ማመንዘር ባገቡ ሰዎች መካከል የሚደረግ ሕጋዊ ያልሆነ ወሲብ ሲሆን ዝሙት ግን ባላገቡ ሰዎች መካከል የሚደረግ ወሲብ ነው። ርኩሰት፥ አንድን ሰው እንዲረክስ የሚያደርገው የልብና የአእምሮ እድፈት ነው። ለርኩስ ሰው ሁሉም ነገር የሚታየው ቆሻሻ መስሎ ነው (ቲቶ 1፡15 ተመልከት)። መዳራት በሥነ ምግባር ዝቅተኛነት የተነሣ ዝሙት ማብዛት ሲሆን ምንም ዓይነት ኀፍረት የማያግደው ልቅ ፍላጎት ነው። እነዚህ ኃጢአቶች በሙሉ በሮም መንግሥት ግዛት ውስጥ ከቁጥጥር ውጭ እንደ ነበሩ የታወቀ ነው። ስካርና ዘፋኝነት ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው አይደሉም።

(2) የጣዖት አምልኮ ኃጢአቶች (5፡20)

ጣዖትን ማምለክ ከላይ እንደ ተገለጹት ኃጢአቶች ዛሬም ከእኛ ጋር አለ። ጣዖትን ማምለክ በቀላል አባባል አንዳንድ ነገሮችን ከእግዚአብሔርና ከሰው ማስቀደም ነው። እግዚአብሔርን ማምለክ፥ ሰዎችን መውደድና በነገሮች መጠቀም ኃላፊነታችን ነው። እኛ ግን ብዙ ጊዜ ሰዎችን እንጠቀምባቸዋለን፤ ራሳችንን እንወዳለን፤ ነገሮችን እናመልካቸዋልን። እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ከጉዳያችን እናስወጣዋለን። ኢየሱስ የምናመልከውን እንደምናገለግል ተናግሯል (ማቴ. 4፡10)። ክርስቶስን ከማገልገል ይልቅ ለመኪናው፥ ለቤቱ፥ ወይም ለጀልባው ቅድሚያ የሚሰጥ ክርስቲያን ጣዖትን ወደማምለክ አደጋ ላይ ይገኛል (ቆላ. 3፡5)።ፋርማኪያ ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘው ጥንቆላ ወይም ምዋርት የሚለው ቃል

«መድሃኒቶችን መጠቀም» ማለት ነው። ፋርማሲ የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የተገኘውም ከዚህ ነው። በጳውሎስ ዘመን የነበሩ ምዋርተኞች ክፉ የሆነ ተግባራቸውን ለመፈጸም ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙት በመድኃኒቶች ነበር። በእርግጥ ጥንቆላ ወይም ምዋርት እንደ ሌሎች የአስማት ተግባራት ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተከለከለ መሆኑ ተገልጿል (ዘዳ. 18፡9-22)።

(3) ማኅበረሰባዊ ኃጢአቶች (5፡20-21)

ጥላቻ «ጠላትነት» ሌሎችን የማንቋሸሽና የመናቅ የአእምሮ ዝንባሌ ነው። ይህ ዝንባሌ የጠላትነት ተግባራዊ መግለጫ ወደሆነው ልዩነትና ሁከት ያመራል። ቅንዓት ቀናተኛነት ወይም ባላንጣነት ነው። ክርስቲያኖች እርስ በርስ ሲፎካከሩና በሌሎች ፊት አንዱ ሌላውን መጥፎ አድርጎ ሲያቀርብ ማየት እንዴት የሚያሳዝን ነው! ቁጣ የስሜት መገንፈልን የሚያሳይ ሲሆን፥ አድመኛነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈልን የሚፈጥር፥ ለራስ ብቻ የመስገብገብን ፍላጎት ያንጸባርቃል።

መለያየትና መናፍቅነት ተወራራሽ ቃሎች ናቸው። የመጀመሪያው የመከፋፈል አሳብ ያለው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በድርጅታዊ መንፈስ የሚፈጠር የቡድን አሠራርን ያንጸባርቃል። ስለዚህ መከፋፈልና መለያየት የሚሉት ቃሎች የተሻሉ ትርጉሞች ናቸው። እነዚህ ሁለቱም ባሕሪያት ጌታን ሳይሆን እነርሱን እንድንከተላቸው አጥብቀው የሚጎተጉቱና ራሳቸውን የሚያስተዋውቁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተግባር ውጤቶች ናቸው። (መናፍቅነት ተብሎ የተተረጎመው ሄሪሲ የሚለው የግሪክ ቃል ምርጫን ማድረግ ማለት ነው።) ምቀኝነት የሚለው ቃል ቂም መያዝን የሚያመለክት ሲሆን የሌላን ሰው ንብረት በጥብቅ መፈለግ ማለት ነው (ምሳ. 14፡30)። መግደልና ስካር ተጨማሪ ማብራሪያ አያስፈልጋቸውም።

እነዚህን ኃጢአቶች የሚለማመድ ሰው የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም። ጳውሎስ የሚናገረው ስለ ኃጢአት ተግባር ሳይሆን ስለ ኃጢአት ልማድ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያልተመሠረተ ሐሰተኛ የደህንነት ዋስትና አለ። አማኝ ከጸጋ እንጂ ከሕግ በታች ያለመሆኑ እውነታ ኃጢአት ለመሥራት ምክንያት ሊሆን የሚችል አይደለም (ሮሜ 6፡15)። ይልቁኑ ጌታን በመታዘዝ መኖር ለራስ ብርታት መጨመር ነው።

እንደነዚህ አይነት አስቸጋሪ ኃጢአቶች የማስገኘት ችሎታ ያለው አሮጌው የኃጢአት ተፈጥሮ አንድ አማኝ እንዴት ሊቋቋመው ይገባል? ሕግ

አሮጌውን ተፈጥሮ ሊለውጥ ወይም ሊቆጣጠር አይችልም። አሮጌው ተፈጥሮ መሰቀል አለበት! (ገላ. 5፡24)። ጳውሎስ አግኝ ክርስቶስን በሞቱ፥ በመቀበሩና በመነሣቱ እንደሚመስለው ይገልጻል(ሮሜ 6)። ክርስቶስ ለእኔ ሞቷል፤ እኔ ደግሞ ከእርሱ ጋር ሞቼአለሁ። ክርስቶስ ለእኔ የሞተው የኃጢአቴን ቅጣት ሊያስወግድልኝ ነው፤ እኔ ግን ከክርስቶስ ጋር የሞትሁ የኃጢአትን ኃይል ለመስበር ነው።

ጳውሎስ ይህንን ጉዳይ በገላትያ 2፡19-20 ቀደም ብሎ የገለጸው ሲሆን በ6፡14 ደግሞ እንደገና ያነሣዋል። የሚነግረን ራሳችንን ከመሰቀል ላይ በመቸንከር እንድንሰቅል አይደለም፤ ምክንያቱም ይህ የማይቻል ነው። (አንድ ሰው በራሱ ላይ ሊፈጽማቸው ከማይችላቸው የሞት ተግባራት አንዱ መስቀል ነው።) ጳውሎስ የሚነግረን የሥጋ መሰቀል አንድ ጊዜ ያለቀና የተፈጸመ ጉዳይ መሆኑን ነው። የእኛ ኃላፊነት ይህን አምኖ መራመድ ነው። (በሮሜ 6 ላይ ጳውሎስ ይህንን መቍጠር ይለዋል። ይህንኑ እውነት በቆላ. 3፡5-25 ቀርቦ ትመለከታለህ)።

እኔና አንተ የመንፈስ እንጂ የሥጋ ባለዕዳ አይደለንም (ሮሜ 8፡12-14)። እግዚአብሔር ስለ አሮጌው ተፈጥሮ የሚለውን ነገር መቀበል አለብን እንጂ ያልሆነውን ነው ብለን ማመን የለብንም። ማንኛውንም ምኞቱን እንዲፈጽም ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ በመመገብ ለሥጋ ማሰብ፥ መጨነቅ የለብንም (ሮሜ 13፡14)። በሥጋ ምንም በጎ ነገር የለም (ሮሜ 7፡18)። ስለዚህ በሥጋ መታመን የለብንም (ፊልጵ. 3፡3)። ሥጋ ለእግዚአብሔር ሕግ ሊገዛ (ሮሜ 8፡7)፥ እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኝ (ሮሜ 8፡8) አይችልም። ሥጋ በሰውነታችን የሚሠራውን ሥራ ልንገድል የምንችለው በመንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው (ሮሜ 8፡13)። መንፈስ ቅዱስ የሕይወት መንፈስ ብቻ አይደለም (ሮሜ 8፡2፤ ገላ. 5፡25)፤ የሞት መንፈስም ነው። ራሳችንን ለኃጢአት እንደ ሞትን አድርገን እንድንቆጥር ይረዳናል።

እስካሁን የእግዚአብሔርን መንፈስ ሁለት አገልግሎቶች ተመልክተናል። እነዚህም የፍቅርን ሕግ እንድናሟላና ሥጋን እንድናሸንፍ ማስቻል ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ሦስተኛ አገልግሎትም አለው።

## 3. መንፈስ ቅዱስ ፍሬ እንድናፈራ ያስችለናል (5፡22-23፥ 25-26)

ሥጋን በማሸነፍ ክፉ ነገርን ያለመፈጸም አንድ ነገር ሲሆን መልካም ነገርን ማድረግ ግን ጨርሶ የተለየ ነገር ነው። አንድ ሕግ አክባሪ ሰው በዝሙት ወይም በነፍስ ገዳይነት ተጠያቂ ላይሆን ይችላል (ማቴ. 5፡21-32 ተመልከት)። ነገር ግን እጅግ ውብ የሆኑትን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሕይወቱ ማየት ይቻላልን? አሉታዊ የሆኑ በጎ ነገሮች በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ መኖራቸው በቂ አይደለም፤ አዎንታዊ ብቃቶችም ሊኖሩት ይገባል።

በሥራና በፍሬ መካከል ያለውን ንጽጽር መመልከት አስፈላጊ ነው። በአንድ ፋብሪካ ውስጥ ያለው ማሽን በመሥራቱ የፋብሪካ ውጤቶችን ያስገኛል እንጂ አንዲት የፍሬ ዘለላ እንኳን ማምረት ጨርሶ አይችልም። ፍሬ ሕይወት ካለው ነገር ሊያድግ የሚገባው ነው። ይህም ከአማኙ አንጻር ሲታይ የመንፈስ ሕይወት ነው (ገላ. 5፡25)። «ሥራዎችን» ስናስብ ጥረትን፥ ድካምን፥ ውጥረትንና ልፋትን እናስባለን። «ፍሬን» በምናስብበት ጊዜ ደግሞ ውበትን፥ ጸጥታንና የሕይወትን መገለጥ እናስባለን። ሥጋ የሚያመርተው «የሞቱ ሥራዎችን» ሲሆን (ዕብ. 9፡14) መንፈስ ግን ሕያው ፍሬን ያፈራል። ይህ ፍሬ በውስጡ የበለጠ ፍሬን የሚሰጥ ዘር አለው (ዘፍ. 1፡11)። ፍቅር የበለጠና የተሻለ ፍቅርን ይሰጣል፤ ደስታ ደግሞ የበለጠ ደስታን ያመጣል። የኢየሱስ ትኩረት «ፍሬ የሚያፈራ... አብዝቶ እንዲያፈራ... ደግሞም ብዙ ፍሬ እንዲያፈራ» ነው (ዮሐ. 15፡2፥5)። ምክንያቱም እግዚአብሔርን የምናከብርበት መንገድ ይህ ነው። አሮጌው ተፈጥሮ ፍሬን ማፍራት አይችልም፤ ፍሬን ማፍራት የሚችለው አዲሱ ተፈጥሮ ብቻ ነው።

አዲስ ኪዳን ስለ በርካታ የተለያዩ ፍሬዎች ይነግረናል፤ ከእነዚህም ሰዎችን ለክርስቶስ መማረክ (ሮሜ 1፡13)፥ ቅዱስ አኗኗር (ሮሜ 6፡22)፥ ለእግዚአብሔር ስጦታዎችን ማቅረብ (ሮሜ 15፡26-28)፥ መልካም ሥራዎች (ቆላ. 1፡10)፥ ምስጋና (ዕብ. 13፡15)። በዚህ ክፍል የተዘረዘረው «የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ» ከባሕርይ ጋር የተያያዘ ነው (ገላ. 5፡22-23)። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሆነው በደኅንነትና (የሐዋ. 2፡38፤ 11፡17) ከአገልግሎት ጋር በተያያዙ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

(1ኛ ቆሮ. 12)፥ ከክርስቲያን ባሕርይ ጋር ከተያያዙ የመንፈስ ጸጋዎች ግልጽ ልዩነት መኖሩን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች በስጦታዎቹ ላይ ከሚገባ በላይ በማተኮር የመንፈስን ጸጋዎች ናቅ አድርገው ወይም ቸል ብለው መመልከታቸው የሚያሳዝን ነው። ችሎታዎችን ከማሳየት ይልቅ እውነተኛውን የክርስቲያን ባሕርይ መገንባት መቅደም ያለበት ጉዳይ ነው።

እግዚአብሔር በሕይወታችን የሚፈልጋቸው ባሕርያት በዘጠኙ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ውስጥ ይታያሉ። ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬን ገለጻ ከፍቅር ይጀምራል! ምክንያቱም የቀሩት ፍሬዎች በሙሉ ከፍቅር የሚወጡ ናቸው። የቀሩትን ስምንት ፍሬዎች በቆሮንቶስ ውስጥ ከሚገኙ የፍቅር ባሕርያት ጋር አወዳድር (1ኛ ቆሮ. 13፡4-8 ተመልከት)። በዚህ ክፍል ፍቅርን ለመግለጽ አገልግሎት ላይ የዋለው የግሪክ ቃል «አጋፔ» የሚል ሲሆን ትርጉሙ መለኮታዊ ፍቅር ማለት ነው። (ትርጉሙ «ስሜታዊ ፍቅር የሆነው» «ኤሮስ» የሚለው የግሪኩ ቃል ግን በአዲስ ኪዳን ጨርሶ ጥቅም ላይ አልዋለም።) ይህ መለኮታዊ ፍቅር እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠው ስጦታ ሲሆን (ሮሜ 5፡5) ልናሳድገውና ይበዛልን ዘንድ ልንጸልይ ይገባል (ፊልጵ. 1፡9)።

አንድ ሰው በፍቅር ክልል ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ፥ በውጫዊ ሁኔታዎች ላለመናወጥ ብቃት ያለውን ውስጣዊ ሰላምና ደስታ ይለማመዳል። (ጳውሎስ በፊልጵ. 4፡10-20 የጻፈው ልምምድ እንዲህ አይነት ጉዳይ ነው።) ይህ «የተቀደሰ በጎ አሳብ» በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳ እንዲኖር አስችሎታል። ፍቅርና ደስታ በአንድነት ሰላምን ይፈጥራሉ። ይህም «አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ነው (ፊልጵ. 4፡7)። እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ የሕይወት ብቃቶች ክርስቲያናዊው ሕይወት ወደ አምላኩ ለመቃረብ እያዘነበለ ለመሆኑ ማስረጃዎች ናቸው።

የሚቀጥሉት ሦስቱ ደግሞ የክርስቲያናዊውን ሕይወት ሰብአዊ ዝንባሌ ገጽታ የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህም ትዕግሥት (አንድን ዓላማ ሳይሰለቹና ሳያቋርጡ በብርታት ከግቡ ማድረስ)፥ ቸርነት (የውሃት) እና በጎነት (በተግባር የተገለጠ ፍቅር) ናቸው። ትዕግሥት ያለው ክርስቲያን በቀልን አያደርግም ወይም በሚቃወሙት ላይ ክፉ ነገር እንዲመጣ አይመኝም። እንዲያውም እንዲቀየም በሚያደርገው ነገር ውስጥ እንኳ ደግና የዋህ ይሆናል። ሌሎች ክፉ በዘሩበት ቦታ ሁሉ በጎነትን ይዘራል። የሰው ተፈጥሮ በራሱ ይህንን

ውድድርና መከፋፈል መራ። በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ፍሬ ሊያድግ ጨርሶ አይችልም።

ይህ ፍሬ የተመረተው ለውበቱና ለእይታ ማራኪነቱ ሳይሆን እንዲፀባረቅ ነው። በዙሪያችን ያሉ ሰዎች የፍቅር፥ የደስታ፥ የሰላምና የቀሩት የመንፈስ ጸጋዎች ረሃብተኞች ናቸው። እነዚህን ነገሮች በሕይወታችን ሲያዩ ከእነርሱ ሕይወት የሚጎድል ነገር እንዳለ ይረዳሉ። ፍሬ የምናፈራው እኛው እንድንጠቀምበት ሳይሆን ሌሎች እንዲመገቡትና እርዳታን እንዲያገኙ ነው፤ በዚህም እግዚአብሔር እንዲከበር ነው። ምናልባትም ሥጋ በሕይወታችን ምስጋናን የሚያስገኙ «ውጤቶችን» ሊያመጣልን ይችላል። ነገር ግን ለእግዚአብሔር ክብርን ሊያመጣ የሚችል ፍሬን ሊያፈራ አይችልም። ይህ ትዕግሥትን፥ በመንፈስ መኖርን፥ በብርሃን መራመድን፥ የእግዚአብሔርን ቃል ዘርና ክርስቶስን የማክበር እውነተኛ ፍላጎትን ይጠይቃል።

በአጭሩ ለዚህ ሁሉ ምስጢሩ መንፈስ ቅዱስ ነው። ከኃጢአትና ከራስ ነጻ መውጣት የሆነውን «እምስተኛውን ነፃነት» ሊሰጠን የሚችል እርሱ ብቻ ነው። የፍቅርን ሕግ እንድንፈጽም፥ ሥጋን እንድናሸንፍና ፍሬ እንድናፈራ ያስችለናል።

ታዲያ ራስህን ለእርሱ በመስጠት እንዲሠራ ትፈቅድለታለህን?

## ገላትያ 6፡ 1-10

ወንድሞች ሆይ፥ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ፥ መንፈሳዊያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ። ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ። አንዱ ምንም ሳይሆን ምንም የሆነ ቢመስለው ራሱን ያታልላልና። ነገር ግን እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሥራ ይፈትን፥ ከዚያም በኋላ ስለ ሌላው ሰው ያልሆነ ስለ ራሱ ብቻ የሚመካበትን ያገኛል፤ እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሸክም ሊሸከም ነውና።

ነገር ግን ቃሉን የሚማር ከሚያስተምረው ጋር መልካምን ነገር ሁሉ ይከፋፈል።

አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤ በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና፥ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል። ባንዘልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት። እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ።

# - 11 -

## የፍቅር ነፃነት

«ሳልቬሽን አርሚ» የሚባለው ድርጅት መሥራች ጄኔራል ዊሊያም ቡዝ፥ በአንድ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ በሕመም ምክንያት ለመገኘት ባለመቻላቸው ስለ ላኩት መልእክት ብዙ ጊዜ የሚነገር አንድ ታሪክ አለ። ይኸውም ለጉባኤው ተወካዮች በስልክ ያስተላለፉት መልእክት ነው። መልእክቱ «ሌሎችን» የሚል አንድ ቃል ብቻ ነበር።

«ፒናትስ» በተሰኘ በአንድ የኩምክና ፊልም ውስጥ ሉሲ የተባለች ሴት ቻርሊ ብራውን የተባለውን ሰው «እዚህ ምድር ላይ ያለነው ለምንድን ነው?» ብላ ትጠይቀዋለች። እርሱም «ሌሎችን ለማስደሰት ነው» ብሎ ይመልስላታል። እርሷም ስለ መልሱ ለጥቂት ጊዜ ያህል ካሰበች በኋላ «ለካስ ሌሎቹስ በዚህ ምድር ያሉት ለምንድን ነው?» ብላ ደግማ ትጠይቀዋለች።

በክርስቲያን የቃላት ዝርዝር ውስጥ ቁልፍ ከሆኑ ሐረጎች አንዱ «እርስ በርሳችሁ» የሚለው ነው። «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚለውን ትእዛዝ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ ከአሥራ ሁለት ጊዜያት በላይ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። «እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ» (ያዕ. 5፡16)፥ «እርስ በእርሳችሁ ተመካከሩ» (1ኛ ተሰ. 5፡11)፥ «እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ» (ሮሜ 12፡10)፥ «እርስ በርሳችሁ እንግድነት ተቀባበሉ» (1ኛ ጴጥ. 4፡19) የሚሉት ከሌሎች በርካታ ተመሳሳይ ምክሮች ጥቂቶቹ ናቸው።

በዚህ በምንመለከተው ክፍል ደግሞ ጳውሎስ «አንዱ የሌላውን ሸክም ይሸከም» የሚል ሐረግ ይጨምራል (ገላ. 6፡2)። በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ክርስቲያን ሌሎች ወገኖችን እንዴት ሊያገለግላቸው እንደሚገባ በጥብቅ ያሳስበዋል። በዚህ ክፍል ውስጥ ጳውሎስ ከሌሎች ጋር ልንካፈለው ስለሚገባ ሁለት እጅግ ጠቃሚ አገልግሎቶች ይገልጽልናል።

### 1. ሸክም መሸከም (6፡1-5)

ሕግ አክራሪዎች ሸክም የመሸከም ፍላጎት የላቸውም። በዚህ ምትክ በሌሎች ላይ ሸክምን ይጭናሉ (የሐዋ. 15፡10)። ኢየሱስ በኖረበት ዘመን የነበሩት ፈሪሳውያን አንዱ ኃጢአት ይህ ነበር። «ከባድና አስቸጋሪ ሸክም

ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ፤ እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም» (ማቴ. 23፡4)። ሕግ አክራሪዎች ሁልጊዜ ከራሳቸው ይልቅ በሌሎች ላይ ይጠነክራሉ። በመንፈስ የሚመራ ክርስቲያን ግን ሌሎችን መርዳት እንዲችል ከሌሎች ይልቅ የበለጠ መሥዋዕት ለመክፈል ፈቃደኛ ነው።

ጳውሎስ በድንገት ተሰናክሎ በኃጢአት ውስጥ የወደቀን አንድ ሰው ተምሳሌታዊ ታሪክ ያቀርባል። «ቢወድቅ» የሚለው ቃል ዱብ ዕዳን የሚያመለክት ስለ ሆነ አውቆ አለመታዘዝ አይደለም። ጳውሎስ ይህን መግለጫ የተጠቀመው ለምንድን ነው? ምክንያቱም የሕግ አክራሪዎችን ክፋት ለመግለጽ ኃጢአት በሠሩ ሰዎች ላይ የሚወስዱትን የከፋ እርምጃ ከማጋለጥ የበለጠ ሌላ ማስረጃ ባለመኖሩ ነው። እዚህ ላይ አንዲት አመንዝራ ሴትን ይፈርድባት ዘንድ ወደ ኢየሱስ እየጎተቱ ፈሪሳውያን እንዳመጧት አስታውስ (ዮሐ. 8)፤ ወይም አሕዛብን ወደ ቤተ መቅደስ በማስገባቱ ቤተ መቅደሱን አርክሰሃል ብሎ ጳውሎስን ለመግደል ብጥብጥ ያስነሣውን የአድማ ቡድን አስታውስ (የሐዋ. 21፡27-40)። (ሕግ አክራሪዎች የሚፈልጉት እውነትንና ማስረጃን ሳይሆን ጥርጣሬንና አሉባልታን ነው። የቀረውን የሚያደርገው ተመጻዳቂው ግምታዊ አስተሳሰባቸው ነው።) ስለዚህ በዚህ አንቀጽ ውስጥ ጳውሎስ የሚያነጻጽረው አንድ የተሳሳተ ወንድምን መንፈሳዊ ሰውና ሕግ አክራሪ ሰው እንዴት እንደሚያስተናግዱት ነው።

(1) የአላማ ንጽጽር፡- መንፈሳዊው ሰው ይህንን የተሳሳተ ወንድም በፍቅር ሊያቀናው ሲጥር፥ ሕግ አክራሪዎች ግን ይበልጥ ይጎዱታል። «ማቅናት(ማደስ)» የሚለው ቃል ትርጉም «መረብን መጠገን ወይም የተሰበረ አጥንት መጠገን» እንደ ማለት ነው። ከዚህ በፊት የአጥንት ስብራት ገጥሞህ ከሆነ የተሰበረ አጥንትን መጠገን ምን ያህል ሕመም እንዳለበት ታውቃለህ። ኃጢአትን ያደረገ አማኝ በእውነት ውስጥ የተሰበረ አጥንት እንዳለበት ነውና መጠገን ያስፈልገዋል። በመንፈስ ቅዱስ የሚመራና በጸጋ ነጻነት የሚኖር አማኝ የተሳሳተውን ወንድም ለመመለስ ይጥራል፤ ምክንያቱም «የመንፈስ ፍሬ ፍቅር» ነውና (ገላ. 5፡22)። በፍቅር አንዱ ሌላውን ያገልግል (5፡13)። ኢየሱስ የኃጢአተኞች ሐኪም ለመሆን በፈለገ ጊዜ በፈሪሳውያን ከፍተኛ ነቀፋ ደርሶበት ነበር (ማር. 2፡13-17)። ስለዚህ በዚህም ዘመን መንፈሳዊ አማኝ በሕግ አክራሪዎች ነቀፋ ይደርስበታል።

ሕግ አክራሪ ሰው የተሳሳተውን ወንድም ከማቅናት ይልቅ ይኰንነዋል። የዚህን ወንድም ስህተት በማጉላት የራሱን መልካምነት ለማሳየት ይጠቀምበታል። ኢየሱስ ስለ ፈሪሳዊውና ቀራጩ ሰው በተናገረው ምሳሌ ፈሪሳዊው ያደረገው ይህን ነበር (ሉቃስ 18፡9-14)። «ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ትሸፍናለች» (1ኛ ጴጥ. 4፡8)። አንድ ወንድም በሚወድቅበት ጊዜ ሕግ አክራሪ የሆነ ሰው ደስ ይሰኛል። ብዙ ጊዜም በወሬ ያዛምተዋል። ምክንያቱም ስለ ራሱ መልካምነትና የእርሱም ቡድን የተሳሳተው ሰው ከሚገኝበት ቡድን ምን ያህል የተሻለ እንደ ሆነ በትምክህት ለመናገር የሚችለው ይህን በመሰለው አጋጣሚ በመሆኑ ነው።

ጳውሎስ የተግሣጽን ቃል የተናገረው ለዚህ ነበር። «እርስ በርሳችን እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ» (ገላ. 5፡26)። መነሣሣት ማለት ፍልሚያ ማድረግ፥ መወዳደር ማለት ነው። በመንፈስ የሚመላለስ ክርስቲያን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር አይወዳደርም ወይም «የራሱን ያህል መልካም እንዲሆኑ» አይጎተጉታቸውም። ሕግ አክራሪ ሰው የሚኖረው ግን በውድድርና ራሱን ከሌሎች በማነጻጸር ነው። ሌሎች ወንድሞች መጥፎ እንደ ሆኑ አድርጎ በማቅረብ የራሱን መልካምነት ለማሳየት ይሞክራል።

2. ዝንባሌን የተመለከተ ንጽጽር፡- በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ አማኝ ጉዳዩን የሚያቀርበው በፍቅርና በየዋህነት መንፈስ ነው። ሕግ አክራሪዎች ግን የትምክህትና የመኰነን ዝንባሌ ይዘው ይቀርባሉ። ሕግ አክራሪ ሰዎች እንዲህ አይነቱን ኃጢአት ፈጽሞ ሊሠሩ እንደማይችሉ አድርገው ራሳቸውን ስለሚቆጥሩ ዝንባሌያቸው መልካም አይደለም። በጸጋ የሚኖር አማኝ ግን ማንኛውም ሰው ከኃጢአት ነፃ የሚያደርግ ክትባት እንደ ሌለው ያውቃል። «እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ» (1ኛ ቆሮ. 10፡12)። የራሱን ድካም ስለሚገነዘብ ለሌሎች የትህትና ዝንባሌ አለው።

ነገር ግን ሁለተኛ ተነጻጻሪ ጉዳይ ደግሞ አለ። በልቡ የክርስቶስን ፍቅር ያውቃል። የክርስቶስ ሕግ «እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ» የሚል ነው (ዮሐ. 13፡34፤ 15፡12)። ጳውሎስ ከዚህ ቀደም ብሎ «የፍቅር ሕግን» ገልጦ ነበር (ገላ. 5፡13-15)። አሁን ደግሞ ከሕይወት ጋር ያዛምደዋል። «ርህሩህና ገር የሆነ የፍቅር እንክብካቤ» እንዲኖረን አጥብቆ ስለሚጠይቅ ጉዳዩ በቅርቡ የተገኘ ወይም ሥልጣኔ የወለደው አይደለም። አንድ ሐኪም የተሰበረ አጥንት በሚጠግንበት ጊዜ ርህራሄውንና ገርነቱን ቢያሳየን ምን

ያህል እናደንቀዋለን። እኛም የተሰበረ ሕይወትን ለመጠገን በምንፈልግበት ጊዜ የበለጠ «ርህራሄና ገርነት የሞላበትን የፍቅር እንክብካቤ» ማሳየት ይጠበቅብናል።

በማናቸውም በደል የተገኘን ሰው ለመርዳት መቅረብ ከፍተኛ ፍቅርንና ብርታትን የሚጠይቅ ነው። ኢየሱስ ይህንን ጉዳይ ለዓይን ከሚደረግ ቀዶ ሕክምና ጋር ያወዳድረዋል (ማቴ. 7፡1-5)። ግን ይህን ለማድረግ ብቃት ያለን ስንቶቻችን እንሆን?

ጳውሎስ፥ በዚህ ወቅት እርቅን የመመሥረት አስፈላጊነት በማስመልከት ጌታ ያስተማረው ትምህርት በአእምሮው ሳይኖር አይቀርም (ማቴ. 18፡15-35)። ወንድምህ ቢበድልህ በክርክር አሸናፊ ለመሆን ሳይሆን ወንድምህን ገንዘብህ ለማድረግ ወደ እርሱ ሄደህ በግልህ አነጋግረው። (በዚህ ስፍራ ጳውሎስ «አቅኑት» ብሎ የተጠቀመበት ቃል በ1ኛ ቆሮ. 9፡19-22 ያልዳነን ሰው ለክርስቶስ ስለ መማረክ ከተናገረው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። የጠፉትን ለክርስቶስ መማረክ አስፈላጊ እንደ ሆነ ሁሉ፥ ደህንነት ያገኙትንም ማቅናት አስፈላጊ ነው።) በዚህ እርምጃ ወንድምህ ከሰማህ ጉዳዩ አለቀ ማለት ነው። ሊሰማህ ካልወደደ ግን አንድ ሁለት መንፈሳዊ ሰዎች ከአንተ ጋር እንዲሄዱና እንዲያነጋግሩት ጠይቅ። በዚህ ደረጃ አሻፈረኝ ካለ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በሙሉ ሊያውቀውና የሥነ ሥርዓት እርምጃዎችን ሊወስድበት ግድ ነው። ነገር ግን ኢየሱስ በተጨማሪ የሚጠቁመው ጉዳይ የሥነ-ሥርዓት እርምጃዋ ስኬታማ እንዲሆን ቤተክርስቲያን ጸሎትንና (ማቴ. 18፡19-20)ና ይቅርታ ማድረግን (ማቴ. 18፡21-35) መለማመድ እንዳለባት ነው።

ሕግ አክራሪዎች ለእንደዚህ አይነቱ መንፈሳዊ «ነፍስን መማረክ» ጊዜ እንደሌላቸው እርግጥ ነው። ወንድሙ እንደ በደለ ሲሰማ ወደ እርሱ በመሄድ ፈንታ ይህን ደስ የማያሰኝ ወሬ ለሌሎች በማካፈል ወሬውን ያስፋፋል። (ለሽፋን ያህል ግን ስለ ጉዳዩ በተሻለ ሁኔታ ጠንክሮ ለመጸለይ ነው ይላል።) ያንንም ወንድም መንፈሳዊ አይደለም በማለት መኮነን ይጀምራል።

አስታውስ! እነዚህ ሕግ አክራሪዎች ራሳቸውን የተሻሉ አድርገው የሚያቀርቡት ወንድማቸውን መጥፎ አድርጎ በማሳየት ነው። ስለዚህ ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ማስጠንቀቂያ ይጽፋል (ቁ. 3-4)። የይሁዲነት አቀንቃኞች ስለ ራሳቸው፥ ስለ ውጤታማነታቸውና ወደ ክርስቶስ ስላመጧቸው ሰዎች በትምክህት ስለሚያወሩ ጥፋተኞች ነበሩ (ገላ. 6፡12-14)። ይህንን ብዙ

ጊዜ የሚያደርጉት ራሳቸውን ከሌሎች ጋር በማወዳደር ነበር (2ኛ ቆሮ. 10፡11 ተመልከት)። እንዲህ ዓይነቱ ማወዳደሪያ ግን ኃጢአት የሞላበትና አሳሳች ነው። ከእኛ የባሰ መጥፎ የሆነ አንድን ሰው ማግኘትና ራሳችንን ከእርሱ ጋር በማወዳደር ከእርሱ ይልቅ የተሻልንና ጥሩ የሆንን መስሎ እንዲሰማን ማድረግ ቀላል ነው። የአንድ ወንድም ውድቀት ወይም ድካም እኛን ከእርሱ የተሻልን ሆኖ እንዲሰማን የሚያደርግ ቢሆንም እንኳ የዚያን ወንድም ውድቀት ወይም ድካም ሳንገልጥ እንድንኖር የሚያደርገን ክርስቲያናዊ ፍቅር ነው።

«እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሥራ» ሊፈትን (ገላ. 6፡4) የሚያስፈልገው በእግዚአብሔር ፈቃድ ብርሃን እንጂ በአንድ ሌላ ሰው ስኬታማነት ጥላ ወይም ከለላ አይደለም። «ነገር ግን እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሥራ ይፈትን፥ ከዚያ በኋላ ስለ ሌላው ሰው ያልሆነ ስለ ራሱ ብቻ የሚመካበትን ያገኛል። እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሸክም ሊሸከም ነውና» (ገላ. 6፡4-5)። በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ከኃጢአትና ከሰይጣን ካልተወዳደርን በስተቀር ለውድድር ስፍራ የለም። «ከሁሉ የላቀ፥ ከሁሉ በተሻለ ፍጥነት የሚያድግ፥ እጅግ በጣም ትልቅ፥ መልካም የሚሉ ቃሎች ለክርስቲያናዊ አገልግሎት ጥቅም ላይ ውለው ስንመለከት ክብሩን የሚያገኘው ማን ይሁን ብለን እንጠይቃለን።

ይህ ማለት መረጃ መሰብሰብ ስሕተት ነው ማለት አይደለም። ቻርልስ ሃደን ስፐርጀን ብዙ ጊዜ እንዲህ ይል ነበር፤ «ሥነ አኃዛዊ መረጃን የሚነቅፉ ሰዎች ብዙ ጊዜ የሚዘግቡት ነገር የሌላቸው ናቸው።» እኛ መልካም ሆነን እንታይ ዘንድ ሌሎቹን ከፉ አድርገን ላለማሳየት ግን መጠንቀቅ አለብን። ልክ እንደ ራሳችን አድርገን በሌሎች ስኬታማነትና ባገኟቸው በረከቶች ሐሴት ልናደርግ ይገባናል (ሮሜ 12፡10)። የአካል አንዱ ክፍል የተባረከ ከሆነ አጠቃላይ አካሉ ይባረካልና።

በቁጥር 2 ና 5 ላይ ባሉ አሳቦች መካከል ግጭት የለም። ምክንያቱም፥ «ሸክም» ተብሎ ለተተረጎመው አሳብ አገልግሎት ላይ የዋሉት የግሪክ ሁለት ቃሎች የተለያዩ በመሆናቸው ነው። በቁ. 2 ላይ ያለው እጅግ ከባድ የሆነ ሸክም ሲሆን ቁ. 5 የሚገልጸው ግን «የአንድን ወታደር ትጥቅ» ነው። የሕይወትን ከባድ ሸክም በመሸከም አንዱ ሌላውን ሊረዳ ይገባል። እያንዳንዱ ሰው ለራሱ የሚሸከመው የግል የሕይወት ኃላፊነት ደግሞ አለ። «እያንዳንዱ ወታደር የራሱን ትጥቅ ይሸከም።» መኪናዬ ቢበላሽ በቅርብ

ያለ ወዳጂ ልጆቼን ወደ ትምህርት ቤት በማድረስ ሊረዳኝ ይችላል። እንደ አባት እኔ ብቻ ልወጣው የሚገባኝን ኃላፊነት የመወጣት ግዴታ ግን የለበትም። ልዩነቱ ይህ ነው። በቤቴ ውስጥ አባት የሚሆን ሌላ ሰው ይመጣል ብዬ መጠበቅ የለብኝም። ይህ እኔ ብቻ የምሸከመው ሸክም (እና መብት) ነው።

## 2. በረከቶችን መከፋፈል (6፡6-10)

በቤተ ክርስቲያን ቋንቋ የቃላት ዝርዝር ውስጥ ቁልፍ ከሆኑ ቃሎች «እርስ በእርሳችሁ» የሚለው አንዱ እንደ ሆነ ሁሉ ኅብረት የሚለውም ቃል እንዲሁ ቁልፍ ቃል ነው። በቁጥር 6 ላይ «መከፋፈል» ተብሎ ተተርጉሟል። ቤተ ክርስቲያን ከተቆረቆረችበት ጊዜ ጀምሮ የክርስቲያን ተግባር አንዱ መለያ «አንዱ ለሌላው ማካፈል» የሚል ነበር (የሐዋ. 2፡41-47)። ይህን አሳብ የሚገልጠው ኮይኖኒያ የሚለው የግሪኩ ቃል በእንግሊዝኛውም ሆነ በአማርኛው ትርጉም በሃይማኖታዊ ጽሑፎች ውስጥ በየስፍራው እናገኘዋለን። ትርጉሙ በቀላል አባባል «በጋራ መያዝ» ማለት ሲሆን፥ በክርስቶስ ያለንን የጋራ ኅብረት (ገላ. 2፡9)፥ የጋራ እምነታችንን (ይሁዳ 3)፥ በክርስቶስ መከራ ተካፋይ መሆናችንን ሁሉ ይጨምራል (ፊልጵ. 3፡10)። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኮይኖኒያ የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው ቁሳዊ በረከቶችን ስለ መከፋፈል ነው (የሐዋ. 2፡42፤ 2ኛ ቆሮ. 8፡4፤ ዕብ. 13፡16 [የግሪኩ ቅጂ])። በእነዚህም ቁጥሮች የምንመለከተው በጳውሎስ አእምሮ ውስጥ ያለውን ይህን አንገብጋቢ ነጥብ ነው።

ጳውሎስ መልካም ነገርን እንድንከፋፈል ከሚያዝ ከአንድ ሕግ ይጀምራል (ቁ. 6)። የቃሉ አስተማሪ የሆነ ሰው መንፈሳዊ ሀብትን የሚያካፍል ሲሆን ከእርሱ የሚማሩ ሰዎች ደግሞ ቁሳዊ ሀብታቸውን ማካፈል አለባቸው። (ጳውሎስ የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ለአይሁድ አማኞች እርዳታ ማድረግ እንዳለባቸው ሲገልጽ የተጠቀመበት አቀራረብ ይህ ነበር - ሮሜ 15፡27።) በቁሳዊ ነገሮች የምናደርገው ሁሉ መንፈሳዊ ነገሮችን እንዴት እንደምንመዝን ማስረጃ እንደ ሆነ ልናስታውስ ይገባል። «መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና» (ማቴ. 6፡21)።

ሐዋርያው ጳውሎስ ገንዘብ ላልዳነው ሰው የማሰናከያ ድንጋይ እንዳይሆን ይፈልግ ስለ ነበር ለራሱ መተዳደሪያ የሚሆነውን ሥራ ይሠራ

ነበር (1ኛ ቆሮ. 9 ተመልከት)። ሆኖም ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግሉ መንፈሳዊ መሪ በሕዝቡ ስጦታ መደገፍ እንዳለበት በተደጋጋሚ ያስተምር ነበር። ኢየሱስ «ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል» ብሎ እንደ ተናገረ (ሉቃስ 10፡7) ጳውሎስ የዚህን ዐረፍተ ነገር ስሜት አስተጋብቷል (1ኛ ቆሮ. 9፡11፥14)።

ከዚህ ትእዛዝ በስተ ጀርባ ያለውን መንፈሳዊ መመሪያ መገንዘብ ግን እጅግ አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር አማኞችን ለመጋቢዎችና ለአስተማሪዎች (ለወንጌላውያንም ፊልጵ. 4፡10-19) ቁሳዊ የሆኑ ፍላጎቶቻቸውን ለሚሟያ የሚሆን ነገር እንዲከፍሏቸው ከማዘዙም በተጨማሪ ስጦታንም የሚሰጡ ሰዎች ከፍተኛ በረከት እንደሚያገኙ ገልጿል (ገላ. 6፡7-8)። የመዝራትና የማጨድ መሠረታዊ ሕግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሙሉ ይገኛል። እግዚአብሔር የዘራነውን እንድናጭድ ደንግጓል። ይህ ሕግ ባይኖር ኖሮ «የምክንያትና ውጤት» አጠቃላይ መመሪያ ውድቅ ይሆን ነበር። ስንዴ የዘራ ገበሬ ስንዴ ለማጨድ ይዘጋጃል። ይህ ባይሆን ኖሮ በዓለም ላይ ከፍተኛ ቀውስ ይፈጠር ነበር።

እግዚአብሔር የት እንደምንዘራ እንድንጠነቀቅ ነግሮናል። ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ያተኮረበት መመሪያ ይህ ነው። ቁሳዊ ሀብታችን በሁለት የተለያዩ መሬቶች ላይ ሊዘራ እንደሚችል ዘር አድርጎ ይገልጸዋል። ሁለቱ የተለያዩ መሬቶች ሥጋና መንፈስ ናቸው። ቁሳዊ ንብረታችንን የሥጋውን ወይም የመንፈስን ተግባር ለመፈጸም ልንጠቀምበት እንችላለን። መዝራታችንን ከፈጸምን በኋላ ግን ምርቱን መለወጥ አንችልም።

ለሥጋ የተዘራ ገንዘብ ያለ አግባብ የመበልጸግንና የተገኘውን ብልጽግና ያለ አግባብ የመጠቀምን ውጤት ያመጣል (ገላ. 5፡19-21 ተመልከት)። ይህንንም ገንዘብ አንድ ጊዜ ካወጣነው በኋላ እንደገና መልስ ማግኘት አይቻልም። ለመንፈስ የተዘራ ገንዘብ ግን (ለምሳሌ ቃሉን ለሚያስተምሩ ብለን ማካፈል) ሕይወትን ያስገኛል። በዚያ ምርት ውስጥ እንደገና ሊዘራና ለሌላ ምርት ሊዘጋጅ የሚችል ዘር ያስገኛል። ይህም ዑደት እስከ ዘለዓለም ድረስ ይቀጥላል። እያንዳንዱ አማኝ ቁሳዊ ሀብቱን እንደ ዘር ቢቆጥርና በሚገባ ቢዘራው በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ የገንዘብ እጥረት ሊኖር አይችልም። ብዙ ዘሮች የሚባክኑት በሥጋዊ ነገሮች ስለ ሆነ ለእግዚአብሔር ክብርን ሊያመጡ ያለመቻላቸውን መመልከቱ ያሳዝናል።

ይህንን መመሪያ ከሕይወታችን ጋር በማዛመድ ተግባራዊ የምናደርግበት ከዚህ የላቀ መንገድ መኖሩ አያጠራጥርም። ምክንያቱም የምናደርገው ነገር ሁሉ በሥጋ ወይም በመንፈስ ላይ የምናፈሰው መዋዕለ ነዋይ ሆኖ ስለሚቆጠር የዘራነውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ እናጭዳለን። የምናጭደውም በዘራንበት መጠን ነው። «በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፥ በበረከት የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል» (2ኛ ቆሮ. 9፡6)። በመንፈስ የሚመላለስና በመንፈስ የሚዘራ አማኝ መንፈሳዊ ምርትን ያጭዳል። አዘራሩ በበረከት ከሆነ ምርቱም በዚህ ሕይወት እንኳ ባይሆን በሚመጣው ዘለዓለማዊ ሕይወት የተትረፈረፈ ይሆናል።

የጳውሎስ ጠላቶች የነበሩት የይሁዲነት አቀንቃኞች በመስጠትና በመቀበል ጉዳይ እንዲህ አይነት መንፈሳዊ ዝንባሌ አልነበራቸውም። ጳውሎስ ለኑሮው ሲል በሥራ መጠመዱና ላቡን ማፍሰሱ ለቤተ ክርስቲያን ሸክም ላለመሆን ነበር። ሐሰተኛ አስተማሪዎች ግን አብያተ ክርስቲያናትን የራሳቸውን እቅድ ለማስፈጸምና ሳጥናቸውን ለመሙላት ተጠቅመውባቸዋል። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተፈጸመውና ጳውሎስን የሚከተለውን መልእክት ይጽፍ ዘንድ ያደረገው ይህ ዓይነቱ አድራጎት ነበር። «ማንም ባሪያዎች ቢያደርጋችሁ ማንም ቢበላችሁ፥ ማንም ቢቀማችሁ፥ ማንም ቢኮራባችሁ፥ ማንም ፊታችሁን በጥፊ ቢመታችሁ ትታገሡላችሁና» (2ኛ ቆሮ. 11፡20)

ሥርዓት የለሽ የሆነውና የገዛ ጥቅሙን የሚያስፋፋው ሰው ሲከበርና የሚፈልገውን ነገር ሁሉ ሲያገኝ፥ ታላቅ መስዋዕትነትን በመክፈል በፈሪሃ እግዚአብሔር የሚሠራ መጋቢ ሲሰደድና ተገፍቶ ሲወጣ ያየነው ምን ያህል አየተናል? ሥጋዊ ለሆነው አማኝ «መንፈሳዊ አምባገነንነትን የሚያራምደውና የሕግ አክራሪነቱ የታወቀው መጋቢ አመራር ያረካዋል። ምክንያቱም በዚህ ሰው አመራር ሥር ዋስትና ያለው፥ ስኬታማና መንፈሳዊ ሰው የሆነ ስለሚመስለው ነው። ሥጋዊ አማኝ ሊፈጽመው የፈለገው ተግባር የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን ያለውን ሁሉ ለማካፈል ወደ ኋላ ባይልም ዳሩ ግን የዘራው ለሥጋው እንጂ ለመንፈስ ያለመሆኑን ውሎ አድሮ ይገነዘባል።

ጳውሎስ ትእዛዙንና (ገላ. 6፡6) በትእዛዙ ሥር ያለውን መመሪያ (ቁ. 7ና 8) ከሰጠ በኋላ ቀጥሎ አንድ ተስፋን ይሰጠናል (ቁ. 9)፤ «ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና።» ከዚህ ተስፋ በስተጀርባ አንድ አደጋ አለ፤ ይህ

አደጋ በጌታ ሥራ ውስጥ ድካምን ማሳየትና በመጨረሻም ጉልበት አጥቶና ራስን ስቶ አገልግሎትን ማቆም ነው።

የመንፈሳዊ ጉልበት ማጣትና መሳት አንዳንድ ጊዜ ምክንያቱ ለጌታ ሙሉ ለሙሉ ያለመሰጠት ነው። «በሥራ፥ በድካምና በትዕግሥት» አንጻር የተመሰገኑትን ሁለት አብያተ ክርስቲያናት በንጽጽር መመልከት ጠቃሚ ነው (1ኛ ተሰ. 1፡3፤ ራእይ 2፡2)። በኤፌሶን የነበረችዋ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ፍቅሯን ትታ ወደ ኋላ ተመልሳ ነበር (ራእይ 2፡4-5)። ለምን? መልሱ ለተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን በተነገረው በጎ ምስክርነት ተሰጥቷል፥ ይህም «የእምነታችሁን ሥራ፥ የፍቅራችሁን ድካም፥ የተስፋችሁን መጽናት» ነው። ዋናዎቹ ተፈላጊ ባሕሪያት ሥራ፥ ድካምና ትዕግሥት ብቻ ሳይሆኑ ተገቢ የሆነ ውስጣዊ መነሣሣት ያለበት «እምነት፥ ፍቅርና ተስፋ» ናቸው። ለጌታ እየሠራን መንፈሳዊ የሆነው የውስጥ መነሣሣታችን እንዲሞት ማድረግ እንዴት ቀላል ነው። ሚልክያስ እንደ ተነበየባቸው የእስራኤል ካህናት ጌታን እያገለገልን «ይህ ድካም ነው» በማለት እናጉረመርማለን (ሚል. 1፡13)።

አንዳንድ ጊዜ ለጌታ ሥራ ታክተን አቅም በማጣት የምንስተው ባለመጸለያችን ነው። «ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው...ነገራቸው» (ሉቃስ 18፡1)። ጸሎት ለመንፈሳዊ ሕይወት ያለው አስፈላጊነት አየር ለሥጋዊ አካላችን የሚያስፈልገውን ያህል ነው። መተንፈስ ብናቆም ራሳችንን ስተን እንወድቃለን። በምግብ እጦት ደግሞ መድከምና ተዝለፍልፎ መውደቅ ይቻላል። «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» (ማቴ. 4፡4)። በሚገባ ሳንመገብና እረፍት ሳናደርግ ለመኖር ብንሞክር አሁንም ራሳችንን ስተን እንወድቃለን። ለእያንዳንዱ ቀን የሚያስፈልገንን ብርታት ለማግኘት «እግዚአብሔርን በመተማመን መጠበቅ» (ኢሳ. 40፡28-31) እጅግ አስፈላጊ ነው።

ጳውሎስ «በጊዜው እናጭዳለንና» በማለት የሚሰጠን ተስፋ ግን ተግተን እንድንቀጥል ይረዳናል። አንድ የተዘራ ዘር ወዲያውኑ ፍሬ እንደማይሰጥ ግልጽ ነው። ለተፈጥሮ ጊዜ እንዳለው ሁሉ ለነፍስም ጊዜ አለው። ስለዚህ ዘሩ ሥር እንዲያወጣና ፍሬ እንዲሰጥ ጊዜ ልንሰጠው ያስፈልጋል። አራሹ አጫጁን ሲያገኘው እንዴት ይደሰታል (አሞጽ 9፡13)። አንድ ቀን

ለማጨድ እንድንችል በየዕለቱ ልንዘራ ይገባናል (መዝ. (126)፡5-6)። ሆኖም የመከሩ ጌታ ባለቤቱ እንጂ አራሾቹ እንዳልሆኑ ማስታወስ አለብን።

በረከቶችን መከፋፈል ቃሉን ከማስተማርና ቁሳዊ ነገሮቻችን ከመስጠት ሁሉ የላቀ ነገር ነው። ይህ «ለሰው ሁሉ» መልካም ማድረግን ይጨምራል (ገላ. 6፡10)። በዚህ ዓለም ላይ ክፉ የሚያደርጉ ሰዎች አሉ (መዝ. (34)፡16)። ለመልካም እንኳ ክፉ የሚመልሱ ሰዎች አሉ (መዝ. (35)፡12)። በዓለም ላይ የሚኖሩ አብዛኞዎቹ ሰዎች ለበጎ በጎን ለክፉ ክፉን ይመልሳሉ። (1ኛ ተሰ. 5፡15፤ ሉቃስ 6፡32-35 ተመልከት)። ክርስቲያን ግን ለክፉ እንኳ በጎን መመለስ ይጠበቅበታል (ሮሜ 12፡18-21)። ይህንንም በክርስቲያናዊ ፍቅር አንጻር ልናደርገው ይገባል። የክርስቲያን መልካም ሥራዎች ለጌታ የሚሠዋቸው መንፈሳዊ መሥዋዕቶች ናቸው (ዕብ. 13፡16)።

«ለሰው ሁሉ መልካም» ልናደርግ ይገባል። ብርሃናችን እንዲበራና በሰማይ ያለው አባታችን እንዲከበር የምናደርገው በዚህ ዓይነት ነው (ማቴ. 5፡16)። ለማያምኑ ሰዎች የምንመሰክረው በቃላቶች ብቻ ሳይሆን በሥራዎችም ጭምር ነው። ሥራዎቻችን የቃል ምስክርነታችንን መንገድ የቀና ያደርጉታል። የተሰሚነት ሥልጣን እንዲኖረን ያደርጋሉ። ይህ ማለት ደግሞ የምንሠራው ሁሉ «ይህ ሰው የእኔ እርዳታ ማግኘት ይገባዋልን?» ብለን በመጠየቅ መሆን የለበትም። እኛስ እግዚአብሔር በክርስቶስ ያደረገልን ነገር የሚገባን ነውን? ራሱን ለመከላከል እንደ ሞከረው የሕግ ሰው «ባልንጀራዬ ማን ነው?» ብለን ክርክር የምንከፍትበትም ጉዳይ አይደለም (ሉቃስ 10፡25-37)። ኢየሱስ ይህን ለመሰለው ጉዳይ የምናቀርበው ጥያቄ «ባልንጀራዬ ማን ነው?» የሚል ሳይሆን «ለማን ባልንጀራ መሆን እችላለሁ?» የሚል መሆን እንዳለበት ግልጽ አድርጎልናል።

ለሰው ሁሉ መልካም በምናደርግበት ጊዜ «ለሃይማኖት ቤተሰዎች»፥ ለአማኞች ኅብረት ቅድሚያ መስጠት አለብን። ይህ ማለት ደግሞ አንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ከአካባቢዋ ትለይ ወይም አባሎችዋ ሌሎችን ለመርዳት አንዳችም ነገር አያድርጉ ማለት አይደለም። ይልቁኑ ሚዛናዊ የመሆን ጉዳይ የሚጠይቅ ነው። በጳውሎስ ዘመን የነበሩ አማኞች በውጭ ካሉ ይልቅ በርካታ ነገሮች የሚያስፈልጋቸው ነበሩ። ምክንያቱም ብዙዎቹ አማኞች ለእምነታቸው መከራን እየተቀበሉ ነበር (ዕብ. 10፡32-34

ተመልከት)። በተጨማሪ ሰው በጎረቤቱ ላሉ ሰዎች ከማሰቡ በፊት ለራሱ ቤተሰብ ሁልጊዜ ማሰብ አለበት (1ኛ ጢሞ. 5፡8)።

ሆኖም ግን ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያለንን የምንከፋፈለው፥ ሁላችንም ከችግር ለማትላቀቀዋ ለዚህች ዓለም ማካፈል እንችል ዘንድ ነው። በሃይማኖት ቤተሰብ ውስጥ የሚገኝ ክርስቲያን ለማስተላለፍ እንዲችል የሚቀበል ሰው ነው። እርስ በርሳችን በፍቅር ስንገዛ ለሰዎች ሁሉ በፍቅር እንትረፈረፋለን (1ኛ ተሰ. 3፡12)።

መሆንም ያለበት እንደዚህ ነው።

## ገላትያ 6፡11-18

እንዴት ባሉ ታላላቆች ፊደላት በእጄ እንደ ጻፍሁላችሁ እዩ። በሥጋ መልካም ሆነው ሊታዩ የሚወዱ ሁሉ እንድትገረዙ ግድ አሉአችሁ፥ ነገር ግን ስለ ክርስቶስ መስቀል እንዳይሰደዱ ብቻ ነው። በሥጋችሁ እንዲመኩ ልትገረዙ ይወዳሉ እንጂ የተገረዙት ራሳቸው እንኳ ሕግን አይጠብቁም። ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ። በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት መሆን ይጠቅማል እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና። በዚህም ሥርዓት በሚመላለሱ ሁሉ ላይ በእስራኤልም ላይ ሰላምና ምሕረት ይሁን።

እኔ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ስንኳ አያድከመኝ።

ወንድሞች ሆይ፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን። አሜን።

# - 12 -

## የነፃነት መለያዎች

ጳውሎስ አንድን መልእክት በቃል እየተናገረ ጸሐፊ እንዲጽፍለት ካደረገ በኋላ ብዕሩን ወስዶ የራሱን የስንብት ቃል መጻፍ ልማዱ ነበር። እንደ ፊርማ የሆነች የማጠቃለያ ዐረፍተ ነገሩ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን» የምትል ነበረች (1ኛ ተሰ. 5፡28፤ 2ኛ ተሰ. 3፡17-18 ተመልከት)። በዚህ መልእክት ላይ ግን የገላትያ ሰዎች የመልእክቱን አሳብ እንዲያገኙት ለማድረግ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የማጠቃለያ አንቀጹን በሙሉ በገዛ እጁ ነው የጻፈው። «እንዴት ባሉ ታላላቆች ፊደላት በእጄ እንደ ጻፍሁላችሁ እዩ።»

ጳውሎስ ይህን አንቀጽ የጻፈው ለምን ነበር? ደግሞስ ትላልቅ ፊደላትን የተጠቀመው ለምን ነበር? መንፈስ ቅዱስ እነዚህን የማጠቃለያ ቃሎች እንዲጽፍ የመራው በሕግ አክራሪዎችና በመንፈስ ቅዱስ በሚመሩ ክርስቲያኖች መካከል አንድ የመጨረሻ ንጽጽር በማድረግ፥ በመንፈስ የሚመራ አማኝ የሚኖረው ለሰው ምስጋና ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር እንደ ሆነ ለማሳየት ነበር። በትላልቅ ፊደላት የጻፈው ደግሞ «አያምልጣችሁ» የሚል አትኩሮት ለመስጠት ነበር።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቆች የጳውሎስ የሥጋ መውጊያ የአይን ሕመም ችግር እንደ ነበረ ያምናሉ። (2ኛ ቆሮ. 12፡1-10፤ ገላ. 4፡14-15)። ይህ ማለት የጻፈውን ተመልሶ ለማንበብ እንዲችል በትላልቅ ፊደላት መጻፍ ነበረበት ማለት ይሆናል። ይህ ነገር እውነት ቢሆንም ባይሆንም ጳውሎስ ግን ይህን መልእክት በተለየ መንገድ መደምደሙ አንድ ጠቃሚ የሆነ የተለየ ነገር እንዳለው ለማስተላለፍ ማቀዱን ግልጽ ያደርገዋል። የዐይን ችግር ከነበረበት፥ ይህን ማጠቃለያ አንቀጽ በገዛ እጁ ለመጻፍ ፈቃደኛ መሆኑ የአንባቢያኑን ልብ ለመሳብ ሲል ያደረገው ለመሆኑ የተረጋገጠ ነው።

በሕግ ሥር የሚኖር አማኝና በጸጋ ሥር የሚኖር አማኝ በከፍተኛ ሁኔታ እርስ በርሳቸው እንደሚቃረኑ አሳይቶአቸዋል። የቅራኔው መንስዔ «የተለያዩ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች ጉዳይ» ሳይሆን ሁለት የተለያዩ የሕይወት መንገዶች ጉዳይ ነው። ከባርነት ወይም ከነፃነት (ገላ. 5፡1-12)፥ ከሥጋ

ወይም ከመንፈስ (5፡ 13-26)፥ ለራስ ወይም ለሌሎች ከመኖር (6፡ 1-10) መምረጥ ነበረባቸው።

አሁን አራተኛውን ማነጻጸሪያ ያቀርባል፤ ይህም ከሰው ምስጋና ለማግኘት ወይም ለእግዚአብሔር ክብር ሲሉ መኖርን ነው (ገላ. 6፡ 11-18)። ለዚህም መነሻ ነጥቡ ውስጣዊ ዓላማን በማስመልከት ነው። በዚህ ዘመን ባሉ አብያተ ክርስቲያናት የምናገኛቸውን አገልጋዮች ውስጣዊ ዓላማ የመመርመርን ያህል እጅግ አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ የለም። ሁላችንም ብንሆን ምን እያደረግን እንዳለን እናውቃለን፤ ነገር ግን ለምን እንደምናደርገው እናውቅ ይሆን? መልካም ሥራ በመጥፎ ውስጣዊ ዓላማ ይመረዛል።

ጳውሎስ ይህን ጥንቃቄ የሚያስፈልገውን ጉዳይ አስገራሚ በሆነ መንገድ ያቀርበዋል። ሕግ አክራሪ ሰዎች የገላትያ አማኞችን ለግርዘት ሥርዓት እንዲገዙ ለማድረግ ፈልገው ነበር። ስለዚህ ጳውሎስ ይህን ጉዳይ በመውሰድ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከሠራው ሥራና ከራሱ አገልግሎት ጋር ያያይዘዋል። በዚህ አንቀጽ ውስጥ ጳውሎስ፥ ሦስት ሰዎችን ለይቶ ያቀርባል። እነርሱም ሕግ አክራሪ የሆነ ሰው (6፡ 12-13)፥ ኢየሱስ ክርስቶስና (6፡ 14-16) ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱ (6፡ 17-18) ናቸው።

## 1. ሕግ አክራሪ ሰው (6፡ 12-13)

ጳውሎስ ስለ ሕግ አክራሪ ሰው የሚናገረው አንዳችም በጎ ነገር የለውም። ይህን ሰውና መሰሎቹን በአራት የተለያዩ መንገዶች ይገልጻል።

በመጀመሪያ ፎካሪዎች ናቸው (6፡ 12-13)፡- ዋና ዓላማቸው ሰዎችን ለክርስቶስ መማረክ ወይም አማኞች በጸጋ እንዲጸኑ መርዳት እንኳ አይደለም። ዋና ዓላማቸው ብዙ ሰዎችን በትምህርታቸው መለወጥና ስለዚሁ ስላደረጉት ነገር መፎከር ነበር። በውስጣቸው አንዳችም መልካም ነገር ባይኖራቸው እንኳ «በውጫዊ ገጽታቸው መልካም ሆነው ሊታዩ» ይፈልጉ ነበር። ተግባራቸው ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ወይም ለእግዚአብሔር ክብር ሳይሆን ለራሳቸው ክብር ነበር።

ሰዎችን ለክርስቶስ መማረክ ወይም የእግዚአብሔር ሥራ ሲያድግና ሲጨምር ማየት ስህተት እንዳልሆነ ግልጽ ቢሆንም፥ እነዚህን ነገሮች ለሰው ክብር ማስገኛ እንዲሆኑ መፈለግ ግን በማያሻማ ሁኔታ ስህተት ነው። ሰዎችን በመንፈሳዊ አገልግሎታችን ላይ በብዛት ተካፋይ እንዲሆኑ የምንፈልገው

ለቁጥራቸው ማደግ ስንል ሳይሆን ሰዎች ዋጋ ስላላቸው ነው። ሰዎችን ለግላችን የስግብግብነት እቅድ ማሚያና ለክብር ማስገኛ ስንል ልንጠቀምባቸው አይገባም።

የበርካታ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መጽሔቶችንና ጋዜጦች አገኛለሁ። ሆኖም በአንዱ መጽሔት ላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ የሆነው ሰው ሌሎች ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን በስም በመጥቀስ ከእነዚህ ሁሉ የእርሱ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል የተሻለ እንደ ሆነ ለማሳየት የጻፋቸውን ነገሮች ሳይ ደነገጥሁኝ። የሚገርመው ደግሞ ከጠቀሳቸው አብያተ ክርስቲያናት አንዳንዶቹ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት እንኳ አልነበሩም። ስለዚህ ሌሎች ይህንን ትምክህት የሞላበትን ጽሑፍ ሲያነቡ ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል ምን ሊያስቡ እንደሚችሉ በማሰብ አዘንሁኝ። ይህ አንድ መጋቢ ቤተ ክርስቲያናቸውን በመኩነኑ ብቻ ለአባላቱ ዳግመኛ ስለ ክርስቶስ መመስከር እጅግ እንደሚከብድ አያጠራጥርም።

ሁለተኛ፥ አለመግባባትን ለማስወገድ እውነትን እንኳ በሐሰት የሚለውጡ ናቸው (6፡ 12)። ግርዘትንና ከዚህ ሥርዓት ጋር የሚሄዱትን ነገሮች ሁሉ የሚሰብኩትና የሚለማመዱት ለምን ነበር? ስደት እንዳይደርስባቸው በመፍራት ነበር። ጳውሎስ ከጽድቅ ሥራዎች ተለይቶ ያለውን የእግዚአብሔር ጸጋና ደህንነት በመስበኩ ተሰደደ (ገላ. 5፡ 11)። የይሁዲነት አቀንቃኞች በአንድ በኩል ክርስቲያኖችን ክርስቲያኖች እንደ ሆኑ እንዲያስቡ ሲያደርጉ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ለሙሴ ሕግ ተከታዮች ሕግን እንደሚታዘዙ እንዲያስቡ ለማድረግ ይሞክሩ ነበር። ስለዚህ ከክርስቶስ መስቀል ወገን በመቆጠርና ይህም በሕግ ላይ በሚያመጣው ከፍተኛ ጠንቅ ሳቢያ ከሕግ አክራሪዎች ሊደርስባቸው ከሚችለው ስደት አመለጡ።

እኛ ግን ዛሬ ለመስቀሉ (ለክርስቶስ የመስቀል ሞት) ልዩ ፍቅርና አክብሮት አለን። ከዚህም የተነሣ በአንገታችን ወይም በደረታችን ላይ የመስቀል ቅርፅ እናንጠለጥላለን። ለመጀመሪያው ምእተ ዓመት ዘመን ክርስቲያኖች ግን መስቀል ተወዳጅ የጌጥ ዕቃ ከመሆን ምትክ የመጨረሻ ዝቅተኛ ሞትና የውርደት ምልክት ነበር። አንድ ጨዋ የሮም ዜጋ ከሌሎች ጋር በሚወያይበት ወቅት በመሀሉ ስለ መስቀል አንሥቶ ያወራል ማለት ጨርሶ የማይታሰብ ነበር። በአጭሩ መሰቀል ተንቆ የመጣልና የኀፍረት ምልክት ነበር።

ጳውሎስ ክርስቶስን ባመነ ጊዜ ራሱን ከመስቀሉ ጎን በማሰለፍ የሚያስከትለውን ችግር ሁሉ ተቀብሏል። መስቀሉ ለአይሁድ የማሰናከያ አለት፥ ለአሕዛብ ደግሞ ሞኝነት ነበር (1ኛ ቆሮ. 18፡31)። ሕግ አክራሪዎች ከክርስቶስ የመስቀል ሞት ይልቅ በግርዘት ላይ በማተኰር በርካታ ሰዎችን ለመማረክ ችለው ነበር። የሃይማኖት ትምህርታቸው የመስቀሉን ኀፍረት የሚያስወግድ ስለ ነበር በቀላሉ ብዙ ተከታዮች አግኝተው ነበር።

ሦስተኛ፥ ሰዎችን በማግባባት ዘዴ የሚማርኩ ነበሩ (6፡12)። «ግድ አሉአችሁ» የሚለው ቃል ጠንካራ የሆነ የማሳመኛ ክርክርንና ማስገደድንም እንኳ የሚጨምር ነው። ይህ ቃል በገላትያ 2፡14 ላይ «ግድ አልሃቸው» ተብሎ ተተርጒሟል። ሆኖም ግን አገባቡ አንድን ሰው ከፈቃዱ ውጭ በማስገደድ አንድን ነገር ማስፈጸም ለማለት አልነበረም። የይሁዲነት አቀንቃኞች በማግባቢያ ዘዴዎቻቸው ለማሳመን የሚጥሩ ሰዎች ነበሩ። ሕግ አክራሪነት የሕይወት መንገዳቸው እንደ ሆነ ለማሳመን የገላትያን ሰዎች ከማር በለሰለሰ አንደበታቸው ያግባቡአቸው ነበር። ጳውሎስ ግን ቃሉን በተናገረባቸው ስፍራዎች ሁሉ በእውነትና በታማኝነት ይናገር ነበር። በንግግር ችሎታውም ሆነ ወይም በተለያዩ የማሳመኛ ዘዴዎች አልተጠቀመም። (ጳውሎስ ለሚያደምጡት ሰዎች ቃሉን እንዴት ያቀርብ እንደ ነበር ከ1ኛ ቆሮ. 2፡1-5፤ 2ኛ ቆሮ. 4፡1-5 ተመልከት። ጳውሎስ መልእክተኛ ወይም አምባሳደር እንጂ የፖለቲካ ሰው አልነበረም።)

አራተኛ፥ ግብዞች ነበሩ (6፡13)። «ለሕግ እንድትገዙ የሚፈልጉ ቢሆንም እንኳ እነርሱ ለሕግ አይገዙም።» ሕግ አክራሪያን ኢየሱስ «እየተናገሩ አያደርጉትምና» ብሎ ከተናገረላቸው ፈሪሳውያን ተለይተው የሚታዩ አይደሉም (ማቴ. 23፡3)። የጳውሎስ አሳብ የይሁዲነት አቀንቃኞች ሕግን መጠበቅ አለባቸው ማለት እንዳልሆነ ግልጥ ነው። ምክንያቱም ሕግን መጠበቅ አይቻልም፤ ደግሞም አያስፈልግም። ይልቁኑ ጳውሎስ ታማኝ ስላለመሆናቸው ከነናቸው። ደግሞም ግብዞች ነበሩና ቢችሉም እንኳ ሕግን የመጠበቅ ፍላጎት አልነበራቸውም። ለሕግ የነበራቸው ክብር ብዙዎችን ለስውር ዓላማቸው ለመማረክ በሽፋንነት ለመጠቀሚያ ብቻ ነበር። በአባላቶቻቸው ቁጥር አንጻር ከፍ ያለ አኃዛዊ ዘገባን በማቅረብ የላቀ ክብርን ለማግኘት ይፈልጉ ነበር።

አዎን! ሕግ አክራሪ የሆነ ሰው መለያ ምልክት ያለው ነው። ስለዚህ ማንነቱን እንዳወቅህ ከእርሱ ራቅ!

## 2. ኢየሱስ ክርስቶስ (6፡14-16)

ጳውሎስ መልእክቶቹ ስለ መስቀሉ ደግሞ ደጋግሞ ያነሣል (2፡20-21፤ 3፡13፤ 4፡5፤ 5፡11፥ 24፤ 6፡12) «ጽድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ» (2፡21)። ክርስቶስን «የተለየ ሰው» ያደረገው የቀራኒዮ ቁስሎቹ ናቸው። ምክንያቱም በእርሱ ለሚያምኑ ቁስሎቹ ነፃነት ማለት ናቸው። የይሁዲነት አቀንቃኞች በግርዘት ይመኩ ነበር። ጳውሎስ ግን በመስቀል ላይ በሞተውና ከሞት በተነሣው አዳኝ ይመካ ነበር። ለመስቀሉም ልዩ ፍቅርና አክብሮት ነበረው። ይህ ማለት በመስቀሉ ላይ ለተፈጸመው ጭካኔና ሥቃይ ማለት አይደለም። እርሱ ግን መስቀሉን የተመለከተው ወንጀለኞች እንደሚሞቱበት ተራ እንጨት አድርጎ አይደለም። የክርስቶስ መስቀል ትምክህቱ ነበር። ለመሆኑ ጳውሎስ በመስቀሉ የተመካው ለምን ይሆን?

በመጀመሪያ፥ የመስቀሉን ስብእና ያውቅ ስለ ነበር ነው። በገላትያ መልእክት ብቻ ኢየሱስ ክርስቶስ ቢያንስ 45 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። ይህ ማለት ከመጽሐፉ ቁጥሮች አንድ ሦስተኛው እጅ ስለ ኢየሱስ ይናገራሉ ማለት ነው። ጳውሎስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስብእና ፍጹም ተማርኮ ነበር። መስቀሉን ትምክህቱ ያደረገለትም ክርስቶስ ነበር። አይሁዳዊ መምህር ሆኖ ባገለገለባቸው የመጀመሪያ ዓመታት ጳውሎስ ክብርን ሊያገኝባቸው የሚችላቸው በርካታ ሁኔታዎች ነበሩ (ገላ. 1፡13-14፤ ፊልጵ. 3፡1-10)። ክርስቶስን ካመነ በኋላ ግን የነበረውን ክብር እንደ መናኛ ነገር ቆጠረው። ሕግ አክራሪዎች ግን በክርስቶስ ስለማይመኩ በመስቀሉም አይመኩም ነበር። ክብርን የሚሰጡት ለሙሴና ለራሳቸው ነበር። የመስቀሉን ሰው በእርግጥ አላወቁትም ነበር።

ሁለተኛ፥ የመስቀሉን ኃይል ያውቅ ስለ ነበር ነው። በመሠረቱ የተማረ የአይሁድ መምህር ለነበረው ለሳአል፥ በተለይም በመስቀሉ ላይ የተፈጸመን መሥዋእትነት ሃይማኖታዊ ክብደት ይኖረዋል ብሎ መቀበል ጨርሶም የማይታሰብ በሆነ ነበር። መሲሑ ይመጣል ለሚለው ትንቢት ምንም ጥርጣሬ አልነበረውም። ዳሩ ግን የሚመጣው ለመሞት ነው ብሎ ለመገመት፥ ለዚያውም በተረገመ የመስቀል ሞት ይሆናል ብሎ በማሰብ በሳአል የሥነ መለኮት ትምህርት ውስጥ ስፍራ አልነበረውም። በዚያን ዘመን መስቀል የደካማነትና የኀፍረት የመጨረሻ ምሳሌ ነበር። ሆኖም የጠርሴሱ ሳአል የመስቀሉ ኃይል ከነካው በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ ሆነ። መስቀሉ የማሰናከያ

አለት መሆኑ ቀረና «ክርስቶስ ለኃጢአታችን ሞተ» ለሚለው መልእክቱ የማዕዘን ድንጋይ ሆነ።

ለጳውሎስ መስቀሉ ማለት ከእኔነት (ገላ. 2፡20)፥ ከሥጋ (5፡24)ና ከዓለም (6፡14) ነፃ መውጣት ማለት ነው። በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የእግዚአብሔር ኃይል ለአማኞች ነፃነትና ድልን ለማጎናጸፍ ቻለ። አሁን ሕያው ሆነን የምንኖረው እኛ አይደለንም። በእኛ ውስጥ የሚኖረው፥በእኛም በኩል የሚሠራው ክርስቶስ ነው። ራሳችንን ለእርሱ በሰጠን መጠን በዓለምና በሥጋ ላይ ድል እንቀዳጃለን። ለሰው ልጅ በእኔነት፥ በሥጋና በሕግ ላይ ድል የሚሰጥ ኃይል በሕግ ውስጥ እንደሌለ ግልጽ ነው። ከዚህ በተቃራኒ ሕግ የሰውን የእኔነት ስሜት የሚቀሰቅስ (እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት አንድ ነገር ማድረግ እችላለሁ» እና ሥጋ እንዲሠራ የሚያበረታታ ነው። ዓለም መስቀሉን እስካልተከተለች ድረስ «ሃይማኖተኛ» ብንሆን ባንሆን ግድ የላትም። እንዲያውም ዓለም ከኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የተለየ ሃይማኖትን ታበረታታለች። ስለዚህ ሕግ አክራሪ የሆኑ ሰዎች ራስ ወዳድነትን ከፍ ያደርጋሉ፤ ሥጋን ያቀላምጣሉ፤ ዓለምን ደግሞ ያስደስታሉ። እውነተኛ ክርስቲያን ግን ሦስቱንም ይንቃል።

ሦስተኛ፥ የመስቀሉን ዓላማ ያውቅ ስለ ነበር ነው። ይህም አዲስ «የእግዚአብሔር ሕዝብን» ወደ ዓለም ለማምጣት ነው። ለብዙ ምእተ ዓመታት የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነበሩ። ሕግ ደግሞ የሕይወት መንገዳቸው ነበር። እነዚህ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት መሰናዶዎች ነበሩ (ገላ. 4፡1-7)። አሁን ግን ክርስቶስ መጥቶ ታላቁን የመዋጀት ሥራ አጠናቋል። በዚህም እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ጎን ትቶ «አዲስ ፍጥረት»እና «የእግዚአብሔር እስራኤል» የሆነውን አዲስ ሕዝብ ወደ ዓለም አምጥቷል። ይህ ማለት እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለውን ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አጠናቋል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር ዛሬ ከአሕዛብም ከአይሁድም «ለስሙ የሚሆንን ወገን» (የሐ. 15፡14) እየጠራ እያወጣ ነው። በክርስቶስ ዘንድ የዘርና የብሔር ልዩነት የለም (ገላ. 3፡27-29)። ጳውሎስ (በሮሜ 11) በግልጽ የሚያስተምረን እግዚአብሔር ለአይሁድ ሕዝብ የወደፊት እቅድ እንዳለው ነው።

የመስቀል አንዱ ዓላማ አዲስ ፍጥረት ማስገኘት ነው (ገላ. 6፡15)። «አዲሷም ፍጥረት» የምትባለው የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን

ናት። «አሮጌው ሰው» በአዳም የሚመራ ፍጻሜው ውድቀት ነው። አዲሱ ፍጥረት ግን በክርስቶስ የሚመራና ስኬታማ የሚሆን ነው።

ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ስለ ሁለቱ አዳሞች (ሮሜ 5፡ 12-21) መሠረታዊ የእምነት ትምህርት ገልጾላቸዋል። የመጀመሪያው አዳም እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ወደ ዓለም ኃጢአት፥ ሞትና ፍርድን አመጣ። የመጨረሻው አዳም (1ኛ ቆሮ. 15፡45) እግዚአብሔርን በመታዘዝ ሕይወትን፥ ጽድቅንና ደኅንነትን አመጣ። አዳም አንድ ኃጢአት ሠራና ፍጥረትን ሁሉ ወደ ፍርድ አስገባ። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞት ፍጹም መታዘዝን በማሳየቱ የዓለም ሁሉ ኃጢአት ዋጋ ተከፈለ። በአዳም ኃጢአት ምክንያት ሞት በዓለም ላይ ነገሠ። በክርስቶስ ድል ምክንያት በክርስቶስ በኩል «በሕይወት መንገሥ» እንችላለን (ሮሜ 5፡ 17)። በሌላ አነጋገር ለመግለጽ አማኝ «የአዲስ ፍጥረት» አካል ነው። ይህ አዲስ ፍጥረት «የአሮጌው ተፈጥሮ» ውሱንነትና ጉድለት አንዳችም ነገር የማይታይበት «መንፈሳዊ ፍጥረት» ነው (2ኛ ቆሮ. 5፡ 17 ተመልከት)።

የመስቀሉ ሌላኛው ዓላማ «የእግዚአብሔር እስራኤል» የሆነውን (ገላ. 6፡ 16) አዲስ ሕዝብን መፍጠር ነው። በአዲስ ኪዳን ስለ ቤተክርስቲያን ከተጠቀሱት በርካታ ስሞች አንዱ ይህ ነው። ኢየሱስ ለአይሁድ መሪዎች እንዲህ አለ፡- «የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ትወሰዳለች። ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች» (ማቴ. 21፡43)። ጴጥሮስም ያንን ሕዝብ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡- «የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» (1ኛ ጴጥ. 2፡9)።

ቀደም ብለን እንደ ጠቀስነው ይህ ማለት በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የእስራኤልን ሕዝብ በዘለዓለማዊነት ተክታለች ማለት አይደለም። ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ ከብዙ ምእተ ዓመታት በፊት ጀምሮ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ ነበረ በዚህ ዘመን ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሕዝብ ናት ማለት ነው።

ለይሁዲነት አቀንቃኞች ይህ ምን አይነት ግሣጼ ነው? ያ ሕግ በእስራኤል ሕዝብ ሊጠበቅ ያልተቻለ የነበረ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያንን ወደ ብሉይ ኪዳን ሕግ ለመመለስ ፈልገው ነበር። ለእግዚአብሔር አዲስ ሕዝብ ለሆነው ለቤተ ክርስቲያን ስፍራ ለመስጠት የእስራኤል ሕዝብ ወደ ጎን ተተወ።

በዚህ ዘመን ያሉ አማኞች በሥጋ «የአብርሃም ልጆች» ላይሆኑ ይችላሉ። በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለ እምነት ግን (ገላ. 4፡28-29) «የአብርሃም ዘሮች» ናቸው። ከሥጋዊ ግርዘት እጅግ የላቀውን ውስጣዊ የልብ ግርዘትን ተለማምደዋል (ፊልጵ. 3፡3፤ ሮሜ 2፡19፤ ቆላ. 2፡1)። በዚህ ምክንያት መገረዝም ሆነ ያለመገረዝ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስገኘው ምንም ውጤት የለም (ገላ. 6፡15፤ 5፡6 ተመልከት)።

3. ሐዋርያው ጳውሎስ (6፡17-18) ጳውሎስ በግርዘት ምልክት የተመካበት አንድ ወቅት ነበር (ፊልጵ. 3፡4-6)። በክርስቶስ ካመነ በኋላ ግን ሌላ ዓይነት ምልክት ያለበት ሰው ሆነ። አሁን ለኢየሱስ ክርስቶስ በሚሰጠው አገልግሎት በደረሰበት ጠባሳና በተቀበለው ሥቃይ ይመካል።

ከሕግ አክራሪዎች ጋር ያለው ተነጻጻሪነት ግልጽ ነው። «የይሁዲነት አቀንቃኞች ምልክት ሊያደርጉብንና ስለዚያም ሊመኩ ይፈልጋሉ። እኔ ግን የኢየሱስን ማኅተም ለክብሩ በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና።» ይህ እንዴት የሚቆጠቁጥ ተግሣጽ ነው! «እንደ እኔ ሃይማኖታዊ መሪዎቻችሁ ለክርስቶስ ክብር ሲሉ የደረሰባቸው ጠባሳ ካለ እስቲ ያሳዩን። ከዚያ በተረፈ ግን በከንቱ አያስቸግሩን!»

ጳውሎስ «አምስቱ የቀራንዮ የሥቃይ ቁስሎች በሥጋዬ ተሸክሜአለሁ» አላለም። ሆኖም በምትኩ ሕግ አክራሪዎች ያልተቀበሉትን መከራ ለክርስቶስ ሲል እንደ ተቀበለ ይገልጻል፤ ይህንንም የሚያረጋግጥበት በሥጋው ላይ ጠባሳ አለው። 2ኛ ቆሮንቶስ 11፡18-33 ስታነብ ይህንን የጳውሎስ አሳብ ለመረዳት አንዳችም ችግር አያጋጥምህም። ጳውሎስ በብዙ ስፍራና በብዙ መንገድ ለክርስቶስ መከራን ተቀብሏል።

በጳውሎስ ዘመን የአረመኔን ጣዖትና አማልእክት የሚከተሉ ሰዎች የጣዖቶቻቸውን ወይም የአማልእክታቸውን ምልክት በሰውነታቸው ላይ ይነቀሱ ነበር። በአማልእክታቸው ስለሚመኩ ሌሎች ይህን እንዲያውቁ ይፈልጉ ነበር። በተመሳሳይ መንገድ ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስ መለያ ተሰጥቶት ነበር። ይህ መለያ ሊጠፋ የሚችል ጊዜያዊ መለያ አልነበረም። እስከ መቃብሩ ድረስ አብሮት የሚሄድ ቋሚ ምልክት ነበር። ይህን ምልክት የተቀበለው ደግሞ በቀላሉ አልነበረም። ለክርስቶስ የተለየ ሰው ይሆን ዘንድ በተደጋጋሚ መከራ መቀበል ነበረበት።

በዚያ ዘመን ባሪያዎችንም መንቀስ የተለመደ ነበር። የባሪያው ጌታ ማን እንደ ሆነ የሚለየውም በዚሁ ንቅሳት አማካይነት ነበር። እንደዚሁ መሆኑን ጳውሎስ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ መሆኑን የማረጋገጥ መለያውን አድርጎ ነበር።

ኃጢአት የሰው ባሕርይ መለያ ምልክት ሊሆን ስለ መቻሉም በዚህ አጋጣሚ ማጤን ይኖርብናል። ኃጢአት በሰው አእምሮ፥ በሰው ሰብእና፥ በሰው አካል ላይ እንኳ ምልክት ማድረግ ይችላል። ኢየሱስ በሚመለስበት ጊዜ አብዛኛ ሰዎች በሚሸከሙት የኃጢአት ምልክቶች አይመኩም፤ ንስሐ መግባትም እነዚያን ምልክቶች አያስወግድም። ክርስቶስ ሲመለስ እነዚህ ለውጦች በሙሉ ተፈጻሚነት ስለሚያገኙ እግዚአብሔር ይመስገን!) ክርስቶስን መውደድ ለእርሱ መኖሪያ ለእርሱ ክብር በተለየ ምልክት መታወቅ እንዴት የላቀ ነገር ነው።

የአሁኑም ዘመን አማኞች ማስታወስ የሚገባቸው ለክርስቶስ መከራን የተቀበለው መሪ ሊያከፍላቸው የሚችለው ነገር ያለው ሰው መሆኑን ነው። በጳውሎስ ዘመን የነበሩ የይሁዲነት አቀንቃኞች መከራን ስለ መቀበል ምንም አያውቁም ነበር። ምናልባት የዚያው ሃይማኖት ቅርንጫፍ ቡድን አባል በመሆናቸው እጅግ መጠነኛ በሆነ መንገድ ስደት ገጥሟቸው ይሆናል። ይህ ግን የክርስቶስ መከራ ተካፋይ ከመሆን ጋር ጨርሶ አይገናኝም (ፊልጵ. 3፡10)።

በምቹ ምሽግ ውስጥ ነዋሪ ሆኖ ከዓለም፥ ከሥጋና ከዲያብሎስ ጋር ስለሚደረግ ትግል አንዳችም ነገር ከማያውቅና ለክርስቶስ መታዘዙን የሚያሳይ ምልክት ከሌለው የሃይማኖት መሪ ተጠንቀቅ። ጳውሎስ ቁጭ ብሎ ትእዛዝ የሚሰጥ አዋጊ መኰንን አልነበረም፤ ወደ ግንባር በመሄድና በኃጢአት ላይ ጦርነት ከፍቶ በመተናነቅ የራሱን ብዙ መከራ የተቀበለ ሰው ነበር።

ጳውሎስ ወደ መልእክቱ ፍጻሜ ሲቀርብ ልክ በጀመረበት መንገድ ያጠቃልላል። ጸጋ! «የሙሴን ሕግ» ሳይሆን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ!

ሁሉም ነገር በዚህ ተጠቃልሏልና ተጨማሪ ነገር መናገሩ አይጠቅምም።